# መጽሔተ ተልእኮ

## ዘማኅበረ ቅዱሳን

## ሚያዚያ ፳፻፲፮ ዓ.ም
## ፩ኛ ዕትም





## ወደ እግዚአብሔር ሕግ ያልቀረበ ማንነት

"ለእኔስ ወደ እግዚአብሔር መቅረብ ይሻለኛል፤ መታመኛዬ እርሱ ነውና።" መዚ. ፸፪፡፳፲



አዘጋጅ
በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በሰንበት ትምህርት ቤቶች ማደራጃ  መምሪያ ማኅበረ ቅዱሳን የሕዝብ ግንኙነትና ትብብር አገልግሎት ማስተባበሪያ

# ማውጫ


01 የማኅበረ ቅዱሳን መልእክት

02 የማንነት ምስቅልቅል

03 ተቋማዊ ለውጥ ዘማኅበረ ቅዱሳን

04 ቤተ አናግድ

05 ግብረ ማኅበረ ቅዱሳን

06 ይናገራል ፎቶው

07 ማኅበረ ቅዱሳን በማእከላት

# 1. የማኅበረ ቅዱሳን መልእክት

ቅድስት ቤተ ክርስቲያን የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል ለዓለም ለማዳረስ ያለ ማቋረጥ አገልግሎት እየሰጠች ትገኛለች። ይህንን ተልእኮዋን ከግብ ለማድረስ እኛ ልጆቿም ፍጹም መንፈሳዊ በሆነ ትጋት ከጎኗ በመሆን ልናገለግል ይገባል። የሰው ልጅ አንዱ የተፈጠረበት ዓላማም አገልግሎት በመሆኑ ጊዜን፣ ገንዘብን፣ ጉልበትን እና ዕውቀትን ለእግዚአብሔር ለመስጠት ፈጽሞ ቸል ልንል አይገባንም። ለዚህም ነው በመጽሐፍ " ታገለግሉት ዘንድ መርጧችኋል እና ቸል አትበሉ።" (መዋ.ዜና.፳፱፥፲፩) ተብሎ የተጻፈልን።

ማኅበረ ቅዱሳን ከተመሠረተበት ጊዜ ጀምሮ የቤተ ክርስቲያንን አገልግሎት በማስፈጸም በኩል ከፍተኛ እንቅስቃሴ እያደረገ ይገኛል። በተለይም የቤተ ክርስቲያንን ተልእኮ ለማሳካት በሚደረገው ጥረት ላይ እንቅፋት የሆኑ ቀዳዳዎችን ለመድፈን ከፍተኛ ጥረት እያደረገ ይገኛል። የግቢ ጉባኤ አገልግሎት፣ የስብከተ ወንጌል አገልግሎት፣የዕቅበተ እምነት ሥራዎች እና የባለ ድርሻ አካላት የእርስ በእርስ ግንኙነቶች ከእነኚህ አገልግሎቶች መካከል ጥቂቶቹ ናቸው።

ዘመኑ የሚጠይቀውን የአገልግሎት ፍላጎት እና ጥራት ከግምት ውስጥ በማስገባት ሲንቀሳቀስ የቆየው ማኅበሩ አባላቱ ቤተ ክርስቲያንን እና ተልእኮዋን በሚገባ ተረድተው እንዲያገለግሉ ለማድረግ በሠራው ከፍተኛ ሥራ ዛሬ ላይ በጎ አስተዋጽኦ ያላቸው ለውጦች እንዲመጡ አስችሏል።

ምንም እንኳን ማኅበሩ ቤተ ክርስቲያን በሁለንተናዊ አቅሟ ተጠናክራ እስክትታይ ድረስ አገልግሎቱን የሚቀጥል ቢሆንም የዘመኑን አካሄድ እና የአገልግሎቱን ፍላጎቱን እየገመገመ የአካሄድ ለውጦችን ማድረግ እንደሚገባው እሙን ነው። ከዛሬ ሦስት ዐሥርት ዓመታት በፊት የነበረው ዘመን እና የሥልጣኔ ደረጃ ዛሬ ላይ በብዙ መልኩ ተቀይሯል።ስለሆነም የማኅበሩም አገልግሎት ከምሥረታው ጊዜ ከነበረው አካሄድ አሁን በተወሰነ መልኩ ለውጦች ያስፈልጉታል።

ይህንን ሐሳብ ተግባራዊ ለማድረግ ማኅበረ ቅዱሳን የተቋማዊ ለውጥ እንቅስቃሴን ከጀመረ ሰነባብቷል።በያዝነው የ2016 ዓ.ም አገልግሎት ዘመን ጥናቱን አጠናቆ ለውጡን ተግባራዊ ለማድረግ እንቅስቃሴ ላይ ይገኛል።

ከላይ እንደተገለጸው ይህ የተቋማዊ ለውጥ ማኅበሩ የሚያከናውነው ተግባር ቤተ ክርስቲያን በዚህ ዘመን የሚያስፈልጋትን የአገልግሎት አካሄድ ከግምት ውስጥ ያስገባ እና የሚታይ ለውጥ የሚያመጣ እንዲሆን የሚያስችለው ይሆናል።በተለይም የባለድርሻ አካላትን (ቤተ ክህነት፣ሰ/ት/ቤት እና ማኅበራት) የተበታተነ የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ወደ አንድ ለማምጣት ማኅበረ ቅዱሳን የድርሻውን የሚወጣበትን መንገድ የሚፈጥር ለውጥ ይሆናል።

ቤተ ክርስቲያን የ10 ዓመት መሪ ዕቅድ በመንደፍ በአስተዳደራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ላይ ለውጦችን ለማድረግ እንቅስቃሴ ላይ ትገኛለች። ማኅበሩም የቤተ ክርስቲያን አንዱ አካል በመሆኑ ይህ የመሪ ዕቅድ ወደ መሬት ወርዶ ለውጥ የሚያመጣ ሥራ እንዲከናወን የራሱን አስተዋጽኦ ማበርከት ይገባዋል። በመሆኑም ተቋማዊ ለውጡ ከዚህ መሪ ዕቅድ ጋር የተናበበ እንዲሆን ለማድረግ ተሞክሯል።

የማኅበሩ አባላት ለተቃማዊ ለውጡ ትግበራ የአንበሳውን ድርሻ መያዝ እንዳለባቸው ግልጽ ነው። በተለይ በአገልግሎት መዋቅሮች ውስጥ የሚገኙ አገልጋዮች ለውጡን በመረዳት እና አስፈላጊነቱን በመገንዘብ የራሳቸውን አስተዋጽኦ ማበርከት ይኖርባቸዋል። ለዚህም ማኅበሩ በየደረጃው በሚገኙ መዋቅሮች አማካኝነት አስፈላጊውን የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮችን የሚያዘጋጅ ይሆናል።

## 2. የማንነት ምስቅልቅሉ መንሥኤና መፍትሔ

በመ/ር ቢትወደድ ወርቁ

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ "ነገር ግን በመጨረሻው ቀን የሚያስጨንቅ ዘመን እንዲመጣ ይህን ዕወቅ፡፡ ሰዎች ራሳቸውን የሚወዱ ይሆናሉና፣ ገንዘብን የሚወዱ፣ ትምክሕተኞች፣ ትዕቢተኞች፤ ተሳዳቢዎች፣ ለወላጆቻቸው የማይታዘዙ፣ የማያመሰግኑ፣ ቅድስና የሌላቸው፣ ፍቅር የሌላቸው፣ ዕርቅን የማይሰሙ፣ ሐሜተኞች፣ ራሳቸውን የማይገዙ፣ ጨካኞች፣ መልካም የሆነውን የማይወዱ፣ ከዳተኞች፣ ችኩሎች፣ በትዕቢት የተነፉ፣ ከእግዚአብሔር ይልቅ ተድላን የሚወዱ ይሆናሉና፡፡" በማለት የዘመኑን ትክክለኛ ገጽታ ይነግረናል፡፡ (2ኛጢሞ.3፣1) በጠቅላላውም ባይሆን በአመዛኙ ያልተጨነቀ የለም፡፡ ዘመን በራሱ ያስጨንቃል ባይባልም በዘመኑ ውስጥ የምንኖር ሰዎች በምንሆነውና በምንፈጽማቸው ድርጊቶች የዘመንን ሁኔታ እንወስናለን፡፡ ዘመን ማለት እያንዳንዳችን ሰዎች ነን፡፡ እንደተባረከ ሰው ሆነን ስንኖር ዘመን ይባረካል፡፡ ክፋትን ስንፈጽምና እርስ በርሳችን ስንገፋፋ ደግሞ ዘመን አስጨናቂ ይሆናል፡፡

የዚህ ዘመን የጭንቀት መንሥኤም ከሰማይ የወረደ ከምድር የፈለቀ ሳይሆን የክፉ ሥራችን ውጤት ነው፡፡ ባለንበት በዚህ ዘመን ያለን ሰዎች የራሳችንን ለማመቻቸት ሌላውን እንንዳለን፤ ራሳችንን ለመካብ የሌላውን እንንዳለን፤ ራሳችንን ብቅ ለማድረግ ሌላውን ዝቅ ማድረግን ሥራችን አድርገነዋል፡፡ ይህ አካሄዳችን ደግሞ መንገዳችንን ጥልፍልፍ ጉዟችንንም ጋሬጣ የበዛበት አድርጎታል፡፡ አያሌ ዘመናትን ለማንኖርበትና ለማንጠቀምበት ነገር ሌላውን እያከሰርንና እጁንና ቤቱን ባዶ እያደረግን የራሳችንን ኪስ ሙሉ ቤታችንንም የሞቀ እናደርጋለን፡፡

ይህን ሁሉ እየፈጸምን ማን ናችሁ? ተብለን ስንጠየቅ ክርስቲያኖች ነን ብለን ስንመልስ አንሸማቀቅም፡፡ ክርስቲያን ማለት ክርስቶስን የሚከተል እንደ እርሱም ፈቃድ የሚመላለስ መሆኑንም እንዘነጋለን፡፡ "በእርሱ እንዳለን በዚህ እናውቃለን፤ በእርሱ እኖራለሁ የሚል እርሱ እንደ ተመላለሰ ራሱ ደግሞ ሊመላለስ ይገባዋል" ተብሎ የተጻፈውንም እንረሳለን፡፡ (1ኛዮሐ. 2፡6) ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ክብር ይግባውና ሰው ሆኖ ሸክማችንን አቅልሎልናል፣ ሕመማችንን ፈውሶአል፣ ከኀዘናችንም አጽናንቶናል፡፡ የክርስትናም መንገድ ጉዞ ከዚህ የተለየ ሊሆን አይችልም፡፡ የሰዎችን ሸክም እንድናቀል፣ ለሰዎችም የኀዘን ምንጭ ሳይሆን የደስታቸው ምክንያት እንድንሆን፣ ለሰዎች የመታወካቸው መነሻ ሳይሆን ለመረጋጋታቸው መንገድ መሆን የክርስትናችን መሠረታዊ መርሕ ነበር፡፡

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እንደ ሚስተዋለው በጭንቀት የምንገላታ፣ ደስታ ርቆን በብስጭት መኖር ሰውነታችንን የተቆጣጠረን፣ በሥራችን በትምህርታችን በትዳራችን መረጋጋት የተሣነን፣ ክፉ ሐሳብ እየተመላለሰብን ከሰው ጋር በሰላም መኖር አቀበት የሆነብን ሰዎች ቁጥር እያሻቀበ ነው፡፡ ከፍ ሲልም ተስፋ በመቁረጥ ራሳቸውን የሚያጠፉ ሰዎች ቁጥር አስደንጋጭ በሆነ መልኩ እየጨመረ ነው፡፡ ለዚህ እንደ ምክንያት ሊነሡ የሚችሉ ሥነ ልቡናዊና ማኅበራዊ መነሻዎች እንደሚኖሩ የታወቀ ቢሆንም በዚህ አጭር ጽሑፋችን ቅዱሳት መጻሕፍትን መሠረት በማድረግ ሁለቱን ያላስተዋልናቸውን መሠረታዊ ጉዳዮችን አሳጥረን እንመልከት፡-

## 2.1 ወደ እግዚአብሔር ሕግ ያልቀረበ ማንነት

ወደ እግዚአብሔር ሕግ መቅረብ ጥቅሙ ከሞት በኋላ ላለው ሰማያዊ ኑሮ ብቻ ሳይሆን በምድርም የሚኖረን አጭር ሕይወታችን ሰላማዊና ፍሬያማ ያደርግልናል፡፡ ልበ አምላክ ክቡር ዳዊት "ለእኔስ ወደ እግዚአብሔር መቅረብ ይሻለኛል፤ መታመኛዬ እርሱ ነውና" ብሎ መናገሩም ለዚሁ ነው፡፡ (መዝ.72፡28) አምላካችን ልዑል እግዚአብሔርም ወደ እኔ ቅረቡ በማለት በነቢያትም ሆነ በሐዋርያት እንዲሁም በመምህራን የሚነግረንም ወደ እርሱ መቅረብና ከእርሱ ጋር እንደ ፈቃዱ መኖር ለሥጋችንም ሆነ ለነፍሳችን፣ ለምድራዊውም ሆነ ተስፋ ለምናደርጋት ለሰማያዊ ሕይወታችን የዋስትና ዋስትና ስለሆነ ነው፡፡ ወደ እግዚአብሔር መቅረብ ስለ እርሱ ፈቃድና በእኛ ላይ ስላለው ዓላማ ከመማር ይቀድማል፡፡ እግዚአብሔርን ዐለማወቅ ማለት ፈቃዱን አለመረዳት ማለት ነው፡፡

በዚህ ዓለም ስንኖር የእግዚአብሔር ፈቃዱ እርሱን እንድናምን እና መጠጊያችንም እንድናደርገው በሰው ያለው ዓላማም መልካም እንደሆነ የእኛም በሰው ላይ ያለን ዓላማ መልካም እንዲሆን ነው፡፡ በቤተ ሰብ፣ በአካባቢ፣ በትምህርት ቤት እና በሌሎችም ተቋማት የምንቀረጽበትና የምንገነባበት ማንነት ከእግዚአብሔር የራቀ ከሆነ ራሳችንንም ሆነ ሰዎችን የምንጎዳ እንሆናለን፡፡ "ከእኔ በቀር ሌሎች አማልክትን አታምልክ፤ የእግዚአብሔር የአምላክህን ስም በከንቱ አትጥራ፤ እግዚአብሔር ስሙን በከንቱ የሚጠራውን ከበደል አያነጻውምና፤ የሰንበትን ቀን ትቀድሰው ዘንድ አስብ፡፡"(ዘፀ. ፳፥፫-፲፯) በሚሉት ሕግጋቱ ስንቀረጽ ማንነታችን እርሱን በማመን ላይ ይመሠረትና ከእርሱ ጋር የሚኖረን የአባትነትና የልጅነት ግንኙኝነት የሠመረ ይሆናል፡፡

የተፈጠርንበትን ዓላማ አዘንግተው የመመለክ ባሕርይ ሳይኖራቸው ከእግራቸው ሥር ከሚያንበረክኩን ባዕዳን አማልክት፣ ጣዖታት፣ ጠንቋዮችና አስማተኞች ያድኑናል፡፡ "አባትህንና እናትህን አክብር፣ አትግደል፣ አታመንዝር፣ አትስረቅ፣ በባልንጀራህ ላይ በሐሰት አትመስክር፣ የባልንጀራህን ቤት አትመኝ፡፡" የሚሉትን ሕግጋት ወደ ቤቱ ቀርበን ስንማር ስናውቃቸውና ስንተገብራቸው ደግሞ ማንነታችን በእርሱ ሕግጋትና ትእዛዛት ላይ የተመሠረተ ይሆናልና፤ ከሰዎች ጋር የሚኖረን መስተጋብር የተስተካከለና ያማረ ይሆናል፡፡ (ዘፀ.20፡1-15) ከሰዎች ጋር ባለን ግንኙነት ማኅበራዊ አኗኗራችንን እያበላሹ ያሉና ምስቅልቅሎችን እየፈጠሩብን ያሉ አጓጉል ልማዶች፣ ክፋቶች፣ ራስ ወዳድነቱ፣ ስግብግብነቱ፣ ግፉ፣ መጠላለፉ፣ ሰውን መጉዳቱ፣ የሰውን ኑሮ በተንኮልና በሤራ ማዘበራረቁ፣ መሰዳደቡ፣ ዘረኝነቱ፣ መቀማማቱ፣ የሰውን ስም ማጠልሸቱ፣ ትዕቢቱ፣ ዕብሪቱ፣ ለጥቅም ሲሉ ሌላውን የመሥዋዕት በግ ማድረጉ ሁሉ መነሻው ከእነዚህ የማኅበራዊ ኑሮ ዋልታ ከሆኑ ሕግጋቱ የራቀ ማንነት ነው፡፡ "አባትህንና እናትህን አክብር" ባለው ቃሉ ያልተመሠረተ ማንነት ያለው ልጅ ወላጁን ያሳፍራል፤ ለወላጆቹ የኀዘን ምንጭ ይሆናል፤ የወላጆቹ ሕመም አይሰማውም፤ በሰዎችም መካከል የተነወሩና የተገለሉ ያደርጋቸዋል፡፡ በየቤቱ በልጆቻቸው የሚያለቅሱ የሚሸማቀቁ ወላጆች የሙብዛታቸው ምክንያትም ይህ ነው፡፡

"አትግደል" በሚለው ክቡር ሕጉ ያልተመሠረተ ማንነት ራሱንም ሆነ ሌላውን በሆነ ባልሆነው ከመግደል አይመለስም፡፡ አትግደል የሚለው ቃል ራስንም ጭምር ከመግደል የሚከለክል ሕግ ነውና፡፡ ይህን ሕግ የማንነትህ መሠረት ስታደርገው ራስህን መግደል አይታሰብህም፡፡ ራሳችንን ለማጥፋት መቻኮላችን ማንነታችንን ዓለም እያቃወሰው ለመሆኑ ትልቅ ማሳያ ነው፡፡ አትግደል በሚለው ሕግ የተመሠረተ ማንነት ለሌላው ቤዛ ስለ መሆን ለሌላው ተላልፎ ለመሰጠት እና ለሌላው ስለ መኖር ያስባል እንጂ ሌላውን ለማጥፋት አያደባም አይፋጠንምም፡፡ የመገዳደላችን ሥረ መሠረት የማንነታችን ከሕጉ መራቅ መሆኑን ልብ እንበል!

የሰው ሚስት እያባበሉ ማሽኮርመም፣ የራስ ያልሆነን ባል በዝሙት ለመጣል መታገሉና ብሎም መጣሉ የመጣው በዚህም አያሌ ትዳሮች የፈረሱት ልጆችም ከወላጆቻቸው ተለያይተው ለልዩ ልዩ የሥነ ልቡና ቀውስ የተዳረጉበት መነሻው "አታመንዝር" የሚለው ሕግ በመዘንጋቱና የማንነታችን ካስማ ባለመሆኑ ነው፡፡ የአመንዝራነት ግብር ሥር ሰድዶ እንደ ቀላል ነገር እንዲታይ ዓለም ትልቅ ሥራ ስለሠራ ተዋደውና "እሰይ አበጀሽ የኛ ልጅ እሰይ አበጀህ የኛ ልጅ" ተብሎ በደስታ የተጋቡ ጥንዶች መጨረሻ የአንዱ ሌላውን ማጥፋት እየሆነ እንደሆነ እየተመለከትን ነው፡፡

ማንነታችን ከእግዚአብሔር ስለ ራቀ መስረቅን ሥልጡንነት አድርገነዋል፡፡ የስንቱን ገንዘብ ሀብት ንብረትና ሰነድ ሰርቀን ሕይወቱንና ኑሮውን አመሰቃቅለናል? በስንቱስ ተሰርቀን ልቡናችን ቆስሏል? ሰርቀን ከስንቱ ጋር ተጋጭተናል? ስንቱን አጋጭተናል? ሰርቀን ስንት ጊዜ ተዋርደናል? ዛሬ የእግዚአብሔር የሆነው ከቤቱ ይሰረቃል፤ የሀገር ሀብት ይሰረቃል፤ ቤተ ክርስቲያን ትሰረቃለች፡፡ ትልቅ የተባለው  ይሰርቃል፤  ትንሹም ይሰርቃል፡፡ በዚህም ምክንያት እየመጣ ያለውን ምስቅልቅል መዘርዘር ጊዜን መፍጀት ነው፡፡

ማንነታችን ከእርሱ ስለተለየ መጽሐፍ መትቶ፣ ስመ እግዚአብሔር ጠርቶ፣ ፍርድ ሸንጎ ቀርቦ እና በዳኞች ፊት ተሰይሞ በሐሰት መመስከር የተለመደ ሆኗል፡፡ በሐሰት ምስክርነት የስንቱ ትዳር ተበትኗል? ስንቱ በግፍ በወኅኒ ተወርውሯል? ስንቱ ከሥራውና ከእንጀራው ተፈናቅሏል ? ስንቱ ሀብቱን ንብረቱን ተነጥቋል ? በዚህስ ምክንያት ስንቱ ራሱንም ሌላውንም አጥፍቷል? ስንቱ የስንቱን ሚስት ሀብት ንብረት ሥራ ሹመትና መዓርግ በመመኘት ስንቱን አሠቃይቷል? ስለሆነም በማኅበራዊ ኑሯችን እየጎዳን እየተጎዳን፣ እየጠፋን እያጠፋን እና እየተጨነቅን እያስጨነቅን ያለው የማንነታችን መሠረቱ ከአምላካችን ከልዑል እግዚአብሔር መራቁ ነውና መንገዳችን የቀና ማኅበራዊ ኑሯችን የሠመረ እንዲሆን ወደ እርሱ እንመለስ፡፡ በተለይ ወላጆች ልጆቻችን ከሕፃንነታቸው ጀምሮ የማንነታቸው መሠረት በሕጉና በትእዛዙ የተመሠረተ እንዲሆን ወደ ቤተ እግዚአብሔር አምጥተን ብናስተምራቸው ሊመጣ ካለው ጥፋት እንደሚድኑ ማስተዋል ይገባናል፡፡ ልበ አምላክ ክቡር ዳዊት "በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ ተተክለዋል፤ በአምላካችንም አደባባይ ይበቅላሉ ያን ጊዜ በለመለመ ሽምግልና ያፈራሉ፤ ደስተኛም ሆነው ይኖራሉ፡፡" በማለት እንደተናገረው፡፡ (መዝ.91፡13-15)

## 2.2 ከእግዚአብሔር ሕግ የራቀ ማንነት

የመጀመሪያው ጭራሹኑ ወደ ሕገ እግዚአብሔር አለመቅረብን ሲያመለክት ይህ ደግሞ ሕገ እግዚአብሔር ከተማሩ በሕጉ በትእዛዙ መኖር ከጀመሩ በኋላ አፈግፍጎ ከሕግ ከትእዛዙ መራቅን ይመለከታል፡፡ ከመጀመሪያው ሁለተኛው የማጥፋት ደረጃው ከፍ ያለ ነው፡፡ ከቤተ እግዚአብሔርም ርቀን ከሕጉም የራቅን እንዳለን ሁሉ በቤቱም እያለን ከሕግ ከትእዛዙ ርቀን በድፍረት ኃጢአት የተያዝን ሰዎች ቁጥር ቀላል የሚባል አይደለም፡፡ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ አንድ ጊዜ ብርሃን ከበራልን በኋላ ማፈግፈግና በዓለም ፈቃድ መውደቅ ውጤቱ ከፉ መሆኑን ሲገልጥ "አንድ ጊዜ ብርሃን የበራላቸውን ሰማያዊንም ስጦታ የቀመሱትን ከመንፈስ ቅዱስም ተካፋዮች ሆነው የነበሩትን መልካሙንም የእግዚአብሔርን ቃልና ሊመጣ ያለውን የዓለም ኃይል የቀመሱትን በኋላም የካዱትን እንደገና ለንስሓ እነርሱን ማደስ የማይቻል ነው" በማለት አስተምሯል፡፡ (ዕብ.6፡4)

ማንነታችንን ከእርሱ ሕግ ባራቅነው ልክ ደፋሮችና የዐዋቂ አጥፊዎች እንሆናለን፡፡ እያወቅን የምናጠፋ ከሆነ ደግሞ ሐዋርያው እንደመሰከረው  እኛን ወደ ንስሓ መመለስ አስቸጋሪ ከፍ ሲልም የማይቻል ነው፡፡ እንደ ይሁዳ ቀርበን ተረድተን መንፈሳዊ ኃላፊነትን ከተቀበልን በኋላ የምንርቅ ሰዎች ፈጣሪያችንን የምንበድልበትን ደረጃ አመላካች፣ በራሳችንና በሌሎችም ላይ የምንፈጥረውን ከፍተኛ ችግር ማሳያ ነው፡፡

ይሁዳ ማንነቱን ከፈጣሪው በማራቁ ምክንያት ከብዙዎች የመረጠውንና ለመንግሥቱም ያጨውን ጌታውን ለመሸጥ በቅቷል፡፡ ማንነታችን ከፈጣሪያችን ሲርቅ እግዚአብሔርን ከመበደል በድፍረትም ከማሳዘን ወደ ኋላ እንደማንል ይሁዳ ምስክር ነው፡፡ ማንነታችን ከሕግ ከትእዛዙ ሲርቅ እየተጓዝንበት ያለው መንገድ ጥፋት እንደሚያመጣብን እየተነገረን እንኳን አንሰማም፡፡ የሚሰጠንንም ምክር ጆሮ ዳባ ልበስ በሚል እናልፋለን እንጂ አንተገብርም፡፡

ጌታችን ይሁዳ አሳልፎ እንደሚሰጠው ቢያውቅም ውሳኔው ግን አልነበረም፡፡ ጌታን አሳልፎ መስጠት የይሁዳ እንጂ የጌታችን ውሳኔ አልነበረም፡፡ በመሆኑም ጌታችን "ነገር ግን የሰው ልጅ አሳልፎ ለሚሰጥበት ለዚያ ሰው ወዮለት፤ ያ ሰው ባልተወለደ ይሻለው ነበር" እያለ ሲናገር እንኳን ይሁዳ ደንግጦ ከጥፋቱ የመመለስ አንዳች ምልክት አላሳየም፡፡ (ማቴ.26፡24) ከእግዚአብሔር ሕግ የራቀ ማንነት የምንላበስ ከሆነ ጥቅማችንን ብቻ እንጂ የሰው መዳንና እግዚአብሔር የሚከብርበት ማናቸውም ነገር ግድ አይሰጠንም፡፡ ይሁዳ ከዝሙት ሕይወት በንስሓ አምልጣ በአልባስጥሮስ ብልቃጥ ሽቶ ይዛ በመምጣት ከክርስቶስ ዘንድ ምሕረትን የተማጸነች ማርያም ባለ ሽቶዋን ተቃምውሟል፡፡ ደቀ መዛሙርቱም በመቆጣት "ይህ ጥፋት ለምንድነው? ይህ በብዙ ዋጋ ተሸጦ ለድሆች ሊሰጥ ይቻል ነበርና" በማለት እንዲናገሩና እንዲቃወሟትም ቀስቅሶ ነበር፡፡ (ማቴ.26፡8)

በዘመናችን የሚስተዋለው በንጹሐን ላይ ማሳደም፣ ዐመፅ እንዲነሣሣ ማድረግ፣ ክፋት የሌለባቸውንም በማታለል የራስ ክፋት መጠቀሚያ ማድረግ ከእግዚአብሔርና ሕግ የራቀ ማንነት መገለጫዎች መሆናቸውን የይሁዳ ማንነት ያስተምረናል፡፡ ከሕገ እግዚአብሔር እቅፍ መውጣት የማንነት ቀውስን ያስከትላል፡፡ ከሕጉ ስንርቅ የሰበሰብነው ይበተናል፤ የቀረበን መልካም ነገር ይርቃል፤ በክብር ፈንታ ውርደት ከደስታ ይልቅ ሥር የሰደደ ኀዘን ውስጥ እንገባለን፡፡ ከሕጉ ስንርቅ ኪሳራ እንጂ አንዳችም ትርፍ አናገኝም፡፡ ለዚህ ምስክር የሚሆነን ከአባቱ ርቆ ወደ ዓለም ተጨልጦና ተገርኝቶ የገባው ልጅ ነው፡፡ (ሉቃ.15፡11-32) ይህ ልጅ ከአባቱ የተቀበለውን ገንዘብ ይዞ ወደ ዓለም ገባ በዚያም ባከነ፤ ገንዘቡንም በአልባሌ ነገሮች በተነ፤ የነበረውንም ሁሉ ከሰረ፤ የዚህም ሁሉ ውጤት ጭንቀት ሆነ፡፡

ወጣቶች ጎልማሶች እስኪ ቆም እንበልና አያሌ ችግር ውስጥ እየከተተን ያለው የጭንቀታችንን መነሻ እንመርምር! ያን ጊዜ ከእግዚአብሔር የራቀ ማንነት ውጤት መሆኑን እናስተውላለን፡፡ ከእግዚአብሔር ሕግ ርቆ የሚሞላ ጉድለት የሚቃና ጥመት የሚስተካከል ዝብርቅርቆሽ የሚገኝ ትርፍ የለም፡፡ ብቻችንን ደከምን እንጂ ድካማችን ያመጣልን ምንም ነገር የለም፡፡ ከሕጉ የመራቅ ውጤት ምን እንደሆነ ከዓለማችንም፣ ከሀገራችንም ከእያንዳንዳችንም ሕይወት እየተማርን ነው፡፡ መራቅ እንደማያዋጣን አስተውለን ወደ አገልግሎታችን ወደ ቀድሞው የንስሓ፣ የምስጋና፣ የትሕትናና የፍቅር ኑሯችን ብንመለስ በብዙ እናተርፋለን፡፡

ልበ አምላክ ክቡር ዳዊት በመዝሙሩ "ጎልማሳ መንገዱን በምን ያነጻል?" በማለት ይጠይቅና አያይዞም ሲመልስ "ሕግህን በመጠበቅ ነዋ!" በማለት ይናገራል፡፡ (መዝ.118፡9) በኃጢአት፣ በዘረኝነትና በጐጠኝነት፣ በትዕቢትና በዕብሪት፣ በክፋትና በማን አለብኝነት፣ በዝሙትና በርኵሰት፣ በስግብግብነትና ለእኔ ብቻ በሚል አስተሳሰብ የቆሸሸ ማንነታችን ሊነጻ የሚችለው ነቢዩ እንደነገረን ሕጉን በመጠበቅ ነው፡፡ ሕጉ ለእግራችን መብራት ለመንገዳችንም ብርሃን ነው፡፡ (መዝ.118፡105) እግራችን በዚህ ዓለም ክፋትና ሥር በሰደደው እግዚአብሔርን የሚዳፈር አስተሳሰብ ተጠልፎ ተሰነካክሏል፤ መንገዳችንም ስርጓጉጥ ሆኖብናል፤ መፍትሔውም ጊዜያዊ እፎይታ የምናገኝበት በሚመስለን ሱስ ውስጥ መደበቅ፣ የአልኮል መጠጥ ውስጥ መሠወር፣ ከዚያም ከፍ ሲል ዛሬ በብዙዎች ዘንድ እንደ ቀልድ እየተዘወተረ እንዳለው ራሳችንን ማጥፋት ሳይሆን ወደ ሕጉ ዘወር ማለት ነው፡፡

ሕጉን ለመጠበቅ የተቸገርንና ሥጋችን እየደጋገመ ወደ ኃጢአት እየጐተተን ያለን ሰዎች ብንኖር እንኳን በፊቱ ተንበርክከን "አምላኬ ለአንተ መገዛት እሻለሁ፤ ሥጋዬ ግን ወደተለማመደው ፈቃዱ ይጐትተኛል፤ አምላኬ ሆይ ስለ እናትህ እንዲሁም የሥጋ ፈቃዳቸውን ድል ስለነሡ ስለ ወዳጆችህ ብለህ የሥጋ ፈቃዴን ድል የምነሣበት ኃይልን ስጠኝ" እያልን እንማጸነው፡፡ ከወዴት እንደወደቅን እናስብ፤ ወደ ቀደመ ፍቅራችንም እንመለስ፡፡

**ይቆየን!**

**ወስብሐት ለእግዚአብሔር!**

# 3. ተቋማዊ ለውጥ ዘማኅበረ ቅዱሳን

ማኅበረ ቅዱሳን እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ በቤተ ክርስቲያን ዕውቅና አግኝቶ ከተቋቋመበት እና ወደ ሥራ ከገባበት ከ1984 ዓ.ም. ጀምሮ እጅግ በርካታ ተግባራትን በቤተ ክርስቲያን ያከናወነ ሲሆን፣ በአባቶች ጥላ ሥር በአገልግሎት በቆየባቸው ያለፉት ሠላሳ ሁለት (፴፪) ዓመታት፣ ቤተ ክርስቲያን ከውስጥና ከውጭ የደረሱባትን ፈተናዎች ተቋቁማ የወንጌል አገልግሎቷን እንድትወጣ ማኅበሩ የራሱን አስተዋጽኦ አበርክቷል፡፡ በተለይም የተማረው የማኅበረሰብ ክፍል ለቤተ ክርስቲያን የራሱን አስተዋጽኦ እንዲያበረክት ያደረገው ጥረት ከፍተኛ ነው፡፡

ሆኖም ተቋማዊና በዓላማ ተነድፎ በቤተ ክርስቲያን ላይ በመንግሥትም ሆነ በሌሎች የእምነት ድርጅቶች እየተደረገ ካለው ተጽዕኖ አንጻር በማኅበሩ እየተደረገ ያለው ጥረት ቤተ ክርስቲያንን በአሸናፊነት እንድትወጣ አላስቻላትም፡፡ በዚህም ሂደት ማኅበሩ ሁሉን አቀፍ ሥልታዊ እንቅስቃሴን ማእከል ያደረገ ጥረት በተደራጀ መልኩ ማበርከት እንዳለበት ለመገንዘብ ችሏል፡፡

በመሆኑም ማኅበረ ቅዱሳን በቤተ ክርስቲያን እየሰጠ ያለውን አገልግሎት ለማጠናከርና የሚፈለገውን ለውጥ ለማምጣት ያስችለው ዘንድ ተቋማዊ ለውጥ ማድረግ አስፈልጎታል፡፡ ይህንንም ተግባራዊ ለማድረግ እንዲያስችለው ከሚከተሉት ተቋማዊ መሠረቶች አነጻር እራሱን በስፋት መመልከት አስፈልጎታል፡፡

## 3.1 የተሰጠውን ተቋማዊ ወሰን (organizational scope)

- ለቤተ ክርስቲያን አስተዳደርና ዘመኑን ለዋጀ አገልግሎት መጠናከር ንቁ ተሳታፊነት ሚናን መውሰድ፣
- "ማኅበሩ በፖለቲካ ጣልቃ አይገባም" የሚለው እንደተጠበቀ ሆኖ ነገር ግን ለቤተ ክርስቲያን ተሰሚነት፣ ተጽዕኖ ፈጣሪነት እና በሀገሪቱ (ልማትም ሆነ ሰላም ወዘተ) ሚና ያላት ተቋም እንድትሆን መሥራት ማለትም ግልጽ አስተምህሮ ላይ የተመሠረተ ተግባር መለየት፣
- ለቤተ ክርስቲያን የህልውና አደጋ ሆነው ጎልተው የወጡትን ችግሮች ለመመለስ፣ ለመከላከልና ለመቋቋም ድርሻውን ወስዶ የመሥራትና ክርስቲያኖችን ለዚህ ማብቃት ማደራጀት፣ ማንቃት፣

## 3.2 ተቋማዊ ጠባይ (organization behavior)

1. ለቤተ ክርስቲያን ተልእኮ መሳካት ኦርቶዶክሳዊ አቅጣጫ አመላካችነት ሁለንተናዊ ድጋፍ፣ ሞጋችነት እና አሳላጭነት ሚና መወጣት፣
2. ከሂደት ተኮር ተግባር (ብዙ የማይለካ) ወደ ውጤት ተኮር የሚለካ ተግባር፣
3. የአገልግሎት ተጠያቂነት የሰፈነበት አገልግሎት ሥርዓት መከተል፣
4. መዋቅራዊ አሠራርና አፈፃፀም ግልፀኝነትን ማጠናከር፣
5. ሚዛናዊ የሆነ ማእከላዊ እና ያልተማከለ አሠራር ሥርዓት፣

## 3.3. የተቋማዊ ዓላማ የትኩረት አቅጣጫ (organizational refocusing)

- የግቢ ጉባኤያትን አገልግሎት መጠናከርና የሚመለከታቸውን ተቋማት አቅም መገንባት
- የትምህርት፣ የሥልጠናና የልህቀት ማእከላት አገልግሎት እና ሌሎች የማሠልጠ አቅም ግንባታን ማሳደግ፣
- ለቤተ ክህነትን አስተዳደር ውጤታማነት መሥራት፣
- የቤተ ክርስቲያን አደጋ ስጋት ቅነሳና መከላከል አገልግሎት (አቅም ግንባታና አደረጃጀት)፣
- ዘላቂናችግር ፈቺ የጥናትና ምርምር አገልግሎት፣
- የተቋማት ግንባታና በባለድርሻዎች መካከል የትብብር አገልግሎት፣
- ተተኪ ትውልድ ለማፍራት አቅሞችን ማልማትና የማያያዝ (developing andconnecting capacities and networking) አገልግሎት መስጠት

## 3.4. ተቋማዊ ቅርጽ አመላካች ርእስ ጉዳዮች

በዚህም ሂደት ማኅበረ ቅዱሳን በቀጣይም አተኩሮ የሚሠራባቸውን የአገልግሎት ዘርፎች ቅደም ተከተል ለመወሰን ይረዳው ዘንድ የሚከተሉትን መስፈርቶች በዋናነት ከግንዛቤ አስገብቷል፡፡

- የቤተ ክርስቲያንን አቅም የሚገነቡ /Capacity Building
- ዘላቂነት /Sustainability
- ተግባራዊ ኦርቶዶክሳዊነት (Ortho-praxi)
- አስተማማኝ የቤተ ክርስቲያንን ህልውና እና ተልእኮ ማስፈፀም የሚያስችሉ/ Reliability
- ዕድገት፣ ጥራት፣ መስፋፋትና መጠናከር የሚያግዙ /Intensity, Extensity and Diffusion
- አሳታፊ አገልግሎት /Participatory
- ተቋም ፈጠራ እና ልማትን የሚያፋጥኑ /Institution Creation and Development
- የአጭር እና የረጅም ጊዜያትን ያማከሉና ትውልድ ተሻጋሪ ለውጦችን /Balancing and Intergenerational/ ናቸው፡፡

**የማኅበሩ ርእይ፣ ተልእኮ፣ ዓላማዎች**

የማኅበሩን አሁናዊ ርእይና ተልእኮ ለማሻሻል ይረዳ ዘንድ የተነሣንበትን፣ አሁን ያለውንና ወደፊት በትኩርት ሊሠራበት የሚጠበቅበትን የአገልግሎት ሂደቶችን ለመረዳት የሚከተሉትን ነባራዊ ሁኔታዎች (የሦስትዮሽ ግንኙነት) ከግንዛቤ ለማስገባት ተሞክሯል፡፡

- ተቋማዊ ርእይ፣ ተልእኮና ዕሴት፤
- ተቋማዊ አቅም፣ ልምድና፤
- የአገልግሎት ከባቢ ነባራዊ ሁኔታ፤

በዚህም ሂደት ዓለም አቀፋዊና ሀገር አቀፋዊ ነባራዊ ሁኔታዎች ከቤተ ክርስቲን የአገልግሎት ተልእኮ አንጻር በስፋት ተቃኝተዋል፡፡ ማኅበሩ የሚከተሉትን አዲስ ርእይ፣ ተልእኮና ዓላማዎች ያቀረበ ሲሆን ለተግባራዊነታቸው እንዲተጉ አስፈላጊውን ክትትልና እገዛ ያለመታከትና ያለመገደብ ለመፈፀም የቆረጠ መሆኑንም ለአባላቱ ያሳውቃል፡፡

## ርእይ

"ቤተ ክርስቲያን ሁለንተናዊ የመሪነት ሚናዋን ስትወጣ ማየት"

ቤተ ክርስቲያን ሁለንተናዊ (ሁለገብ)፤ ማለት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሚና ጎልቶ በሌሎች አካላት ፖሊሲ፣ ዕቅድ ተገቢው ክብር እና ልዕልና (ቦታ) አግኝቶ በማኅበራዊ፣ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊ፣ትምህርት፣ ጤና፣ ሕግ እና ሌሎች ሀገራዊ ጉዳዮች ሁሉ በእምነቱ ተከታይ ጭምር ስትመራ ማየት ማለት ነው፡፡

## ተልእኮ

ለቤተ ክርስቲያን ተልእኮ መሳካት እና ለህልውናዋ የሚተጋ፣ የተደራጀ፣ ምሉዕ ኦርቶዶክሳዊ፣ ርቱዕ ዘመናዊ፣ ሁለገብ መሪ ትውልድ ማፍራት እና ማሰማራት፣

**አስተሳሰብ ወይም ሐሳብ** (thoughught)፤ ኦርቶዶክሳዊ የሆነ አስተሳሰብ ማለት ሲሆን ይኸውም በቅድስት ቤተክርስቲያን ሃይማኖት ላይ የተመሠረተ፣ የእግዚአብሔር የባሕርይ መገለጫዎችን ያገናዘበ፣ የሰው ልጅ የተፈጠረበትን ዓላማ እና እኩልነት፣ ከፈጣሪ በተገኘ ፍጹም ሕግና ሥነ ምግባር የሚመራ፣ ፍቅረ ቢጽ እና ፍቅረ እግዚአብሔር የሞላው፣ከርኩሰት ተለይቶ የሚያስኖር የጠለቀ እና የመጠቀ አስተሳሰብና አስተዳደር፣ ትምህርት፣ ኢኮኖሚ ወዘተ የሚቀረጽበት መሠረት ሆኖ ያገለግላል፡፡

**የተደራጀ ትውልድ**፤ የበረታ፣ የጠነከረ፣ የተደላደለ ለሚጠየቀው አገልግሎት ምላሽ ለመስጠት በግልም ሆነ በጋራ የተሰናዳ ወይም ዝግጁ የሆነ፣ ሲጠሩት አለሁ የሚል፣ ዕውቀት (ሙያን)፣ ገንዘብን፣ ጉልበትን፣ ጊዜን፣ መረጃን አስተባብሮ የተገኘ አርቶደክሳዊ ትውልድ (ቁርጠኛ የቤተክርስቲያን ልጅ ማለት ነው)፡፡

**ለቤተ ክርስቲያን ህልውና የሚተጋ፡-** አማናዊቷ እና ድል አድራጊዋ ቤተ ክርስቲያን የገሃነም ደጆች የማያናውጧት ብትሆንም ሁሌም በፈተና ያለች በመሆኗ በውስጥ እና በውጪ የቅድስት ቤተ ክርስቲያንን ህልውና የሚፈታተናትን ሁሉ በመቋቋም ረገድ ነቅቶ እና ተግቶ የሚሠራ፡፡

**አንድነት መጠበቅ፡-** ክርስቲያን በቅድስት ሥላሴ አምኖ የእግዚአብሔርን ልጅነት ያገኘ፣ በሥጋ ወደሙ የከበረ ኦርቶዶክሳዊ አንደነት ያለው ሲሆን፣ በሀገር ውስጥ እና ከሀገር ውጪ ያለችው ቤተ ክርስቲያን፣ መንፈሳዊ ወይም ምሥጢራዊ አንድነት በአገልገሎት የሚያንጸባርቅ እንዲሁም ዶግማን እና ቀኖናን በጠነቀቀ መልኩ ቤተ ክርስቲያኒቱን እና ልጆቿን የሚጠቅመውን በማቅረብ፣ የሚጎዳውን በማራቅ፣ ከአንድ ሀገር አስተደደራዊ መዋቅር ባለፈ ድንበር የለሽ የአንድነት አስተሳሰብ ማለት ነው፡፡

**ርቱዕ ዘመናዊ፡-** ቀጥተኛ፣ እውነተኛ የሆነ ዘመኑን የዋጀ፣ ከኃጢአት ውጪ ያለውን እና ለሰው ልጆች የሚበጅ የዘመኑን ጥበብ ለይቶ ያወቀ፤

**ምሉዕ ኦርቶዶክሳዊ፡-** በቤተ ክርስቲያኒቱ ትምህርት፣ በዓለሙ ባለው ሙያ የዳበረ፣ ምግባር ሃይማኖት እና አስተሳሰብ የተባበሩለት እና የተዋደዱለት ማንነት ማለት ነው፡፡ በኦርቶዶክሳዊ እወቀት እና ምግባር የተዋሐዱለት፣በተሠማራበት ሁሉ ብቁ ንቁ፣ የተሟላ ማንነት መያዝ ማለት ነው፡፡

**ሁለገብ መሪ ትውልድ፡-** በተሠማራበት ሙያ፣ ሥራ፣ ትምህርት ወዘተ ዘርፎች ሁሉ የመሪነቱን ቦታ የያዘ አርአያነት ያለው የተከበረ እና የተወደደ ትውልድ ማለት ነው፡፡

**ኦርቶዶክሳዊ መንፈሳዊነት፡-** ሕይወትን በእውነት፣በአርአያነት፣ በምሳሌነት፣ በምገባር የሚኖር፣ የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ ከፈቃደ እግዚአብሔር ጋር ስምረት ያለው አኗኗር ማለት ነው፡፡

**የሐሳብ መሪነትን፡-** ኦርቶዶክሳዊ ሐሳቡ በዶግማ ላይ የተመሠረተ፣ የእግዚአብሔርን የባሕርይ መገለጫዎችን ያገናዘበ፣ የሰው ልጆች የተፈጠሩበትን ዓለማ እና እኩልነት፣ ሥነ ምግባሩ ከአምላክ በተገኘ ፍጹም ሕግ የሚመራ፣ ፍቅረ ቢጽ እና ፍቅረ እግዚአበሔርን መሠረት ያደረገ የኑሮ መመሪያን የያዘ፣ በመንፈስ ቅዱስ ገላጭነት ለሚገኝ እውቀት ትልቅ ሥፍራ ያለው፣ በተዋሕዶ እምነት የሚገኝን ሰማያዊ ኑሮን ተስፋ አድርጎ ከኃጢአት እና ርኩሰት ተለይቶ የሚያስኖር የጠለቀ እና የመጠቀ አስተሳሰብ ያለው፡፡

## ዓላማዎች

1. የቤተ ክርስቲያንን ተቋማዊ አስተዳደር የአሠራር ሥርዓትና አስተሳሰብ በቴክኖሎጂ እና በልዩ ልዩ መንገዶች በመደገፍ ዘመኑን ለዋጀ ጠንካሪ አገልግሎት ማብቃት፣

2.በተደራጀ እና ተደራሹን ማእከል ባረገ መንገድ ስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልእኮን ዘርፈ ብዙ በሆኑ መንገዶች በመላው ዓለም ማስፋፋት፣

3. የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተማሪዎችን ሙሉ ስብእናን የሚገነባ ሥርዓተ ትምህርት በማስተማር ዘመኑን የዋጁ ምሉዕ ኦርቶዶክሳዊ የሆኑ በቤተ ክርስቲያን አስተዳደራዊ መዋቅር የሚያገለግሉ እንዲሁም በማኅበራዊ፣ በኢኮኖሚያዊ በፖለቲካዊ እና በሀገር አስተዳደር ጉዳዮች መሪ/ንቁ ተሳታፊ አገልጋዮችን ማፍራት እና ማሰማራት፣

4. በቤተ ክርስቲያን ላይ የሚነዙትን የርእዮተ ዓለም፣ የሐሰት ትርክቶች እና የአፅራረ ቤተ ክርስቲያንን እንቅስቃሴ ጥናትና ምርምር ላይ ተመርኩዞ መሞገት እና የተሳሳቱን በማረም በጠንካራ የዕቅበተ እምነት አገልግሎት የቤተ ክርስቲያንን ህልውና ማስጠበቅ፣

5. የተተኪውን ትውልድ ምንጭ ለማጎልበት የሰ/ት/ቤቶችን አቅም በጠናከር የሕፃናት እና ወጣቶች የተተኪነት ሚና ማሳደግ፣

6. በተመረጡ ገዳማት እና አብነት ትምህርት ቤቶች የልህቀት ማእከል እና የተለየ ክርስቲያናዊ ተልእኮ የሚፈጽሙ እንዲሆኑ የሚያስችል ሁለገብ የአእምሮ ልማት ድጋፍ ማድረግ፣

7. ኦርቶዶክሳዊ መንፈሳዊነትን በተግባር የሚገልጽ ቤተ ሰብ እና አንድነቱን የጠበቀ ኦሮቶዶክሳዊ ማኅበረሰብ በመገንባት የተደራጀ እና የተናበበ አገልግሎት መፈፀም፣

8. ማኅበሩ ዘመኑን የዋጀ ተቋማዊ የአሠራር ሥርዓት በመዘርጋት ተልእኮውን ማሳካት የሚችልበት አቅም መፍጠር (በአመራር፣ በሰው ኃይል፣ በመንፈሳዊነት፣ በግንኙነት፣ በእውቀት፣ በልማት፣ በፋይናንስ፣ በቴክኖሎጂ)

9. ዓለም አቀፍ ግንኙነትና የትብብር አገልግሎት መርሕ ያደረገ የኦርቶዶሳውያንን ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበሪዊና ፖለቲካዊ ተሳትፎ ማሳደግ፣

## ማጠቃለያ

ቤተ ክርስቲያን ውጤታማ አገልግሎት እንድትሰጥ እና ወንጌልን ለዓለም እንድታደርስ እያንዳንዱ ምእመን የድርሻውን ሊወጣ ይገባል። በተለይ በአገልግሎቱ ውስጥ ባለድርሻ አካላት ተብለው የሚጠቀሱት ቤተ ክህነት፣ ሰ/ት/ቤቶች እና ማኅበራት ይህ ጉዳይ በቀጥታ ይመለከታቸዋል፤ ኃላፊነት እና ግዴታም አለባቸው።

ወቅቱ ቤተ ክርስቲያን አገልግሎቷን ለምእመናን እንዳትሰጥ እንቅፋት የሆኑ እጅግ በርካታ ፈተናዎች እየተቃጡበት ያለ ዘመን ነው። ከጊዜ ወደ ጊዜ መጠናቸው እየሰፋ እና ዓይነታቸው እየተቀያየረ የሚመጡትን እነዚህን መከራዎች ለመመከት ዝግጁ የሆነ እንዲሁም አቅም ያለው ትውልድ እና መዋቅር ያስፈልጋል።

ማኅበረ ቅዱሳን የተመሠረተው በቤተ ክርስቲያን ላይ የሚደርሱት መከራዎች በበዙበት እና ምእመናን ሃይማኖታቸውን ለመጠበቅ በተፈተኑበት ወቅት እንደመሆኑ መጠን መፍትሔዎችን ለማምጣት ነው።

ማኅበሩ ቤተ ክርስቲያን የጣለችበትን አደራ ለመወጣት ዘመኑ የሚጠይቀውን የአገልግሎት አካሄድ በመፈተሽ ተስማሚ የአሠራር ሥርዓቶችን መከተል ይገባዋል። የተቋማዊ ለውጡ ዓላማም ይህ ነው። ነገር ግን የአካሄድ ለውጥ ማድረግ ብቻውን በቂ አይደለም።ለተግባራዊነቱ ሁሉም አካላት ተሳትፎ ማድረግ ይኖርባቸዋል።

የማኅበሩ አባላት፣ ግቢ ጉባኤያት፣ የቤተ ክርስቲያን ባለድርሻ አካላት እና ምእመናን ማኅበሩ የጀመረውን የለውጥ ጉዞ በመደገፍ ቤተ ክርስቲያን የተሻለ የአገልግሎት አፈጻጸም እንዲኖራት ማድረግ ይጠበቅባቸዋል።

# 4. ቤተ አናግድ

ሰላም ውድ አንባቢዎቻችን። የዛሬ እንግዳችን ዶ/ር ወሰን አርጋው ይባላሉ። ዶ/ር ወሰን በ1987 ዓ.ም ከቀሲስ እሸቱ ታደሰ ጋር ተጋብተው ሦስት ልጆችን ለማፍራት የቻሉ ሲሆን እርሳቸውም ሆነ ባለቤታቸው ከማኅበረ ቅዱሳን ምሥረታ ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ በአገልግሎት ከሚሳተፉ የማኅበሩ አባላት መካከል የሚጠቀሱ ናቸው። ከእንግዳችን ጋር በአገልግሎት ዙርያ ያደረግነውን ቆይታ ትከታተሉ ዘንድ በአክብሮት እንጋብዛለን።



ዶ/ር ወሰን አርጋው

**መጽሔተ ተልእኮ፡-** በቅድሚያ ጥሪያችንን አክብረው በመምጣትዎ እያመሠገንን ራስዎትን ለአንባብያን ያስተዋውቁልን?

**ዶ/ር ወሰን፡-** ዶ/ር ወሰን አርጋው እባላለሁ። የተወለድኩት ደሴ ከተማ ነው። ዕድሜዬ ለትምህርት ሲደርስ ቤተ ሰቦቼ ወደ ዘመናዊ ትምህርት ቤት አስገቡኝ። ከዘመናዊው ትምህርት ጎን ለጎን ወደ አብነት ትምህርትና ሰንበት ት/ቤት ስላስገቡኝ ጥልቅ እና ረቂቅ ከሆነው የቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ በጥቂቱም ቢሆን ለመካፈል በቅቻለሁ።

**መጽሔተ ተልእኮ፡-** ወደ ማኅበረ ቅዱሳን አገልግሎት መቼና እንዴት ገቡ?

**ዶ/ር ወሰን፡-** ወደ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ስድስት ኪሎ ካምፓስ ስገባ በምስካዬ ኅዙናን ገዳም ተምሮ ማስተማር ሰንበት ትምህርት ቤት መንፈሳዊ ጉባኤ ይዘጋጅ ስለነበር ጉባኤውን የመሳተፍ ዕድል አገኘሁ። የማኅበሩን አገልግሎት ከብላቴ አንድ ዓመት ቀደም ብለን ነበር የጀመርን። ምንም እንኳን በወቅቱ በሕመም ምክንያት ወደ ብላቴ ዘመቻ ባልሄድም ከዘመቻው መልስ ባለው የማኅበረ ቅዱሳን አገልግሎት ውስጥ በተለያዩ የአገልግሎት መስኮች ላይ ተሳትፌያለሁ።

**መጽሔተ ተልእኮ፡-** እርስዎም ሆነ ባለቤትዎ በአገልግሎት በመቆየታችሁ ያገኛችሁት ምንድን ነው?

**ዶ/ር ወሰን፦** እግዚአብሔር ትንሽ ስንቀርበው በብዙ ጸጋና በረከት የሚባርክ አምላክ ነው። ትንሽ ተጠግተነው ብዙ አትርፈንበታል። ትዕግሥትን እንድንማር፣ አእምሮአችን እንዳይናወጽ፣ በቤተ ክርስቲያናችን በደርሱት ፈተናዎች እንድተጋ፣ በጸሎት እንድንበረታ፣ በትንሽ በትልቁ እንዳንረበሽ፣ ሕይወታችን መሥመር እንዲይዝ አድርጎልናል። እግዚአብሔር እንደ ሰው ያዝ ለቀቅ የሚያደርግ አምላክ ባለመሆኑ ሁሌም ይፈልገናል። "ከዚህ የበለጠ ታያላችሁ" ተብሎ እንደተነገረ እግዚአብሔር ከዚህ የበለጠ ሊባርከን እንደተዘጋጀም እናምናለን።

**መጽሔተ ተልእኮ፦** ወጣትነት ፈተና የበዛበት ሕይወት ነው። የወጣትነት ዘመንዎትን እንዴት እንዳሳለፉት ቢነግሩን?

**ዶ/ር ወሰን፦** በልጅነት የተነገረ ቃለ እግዚአብሔር በወጣትነት የሚመጣብንን ፈተና ለማለፍ ያስችላል። እኔም በሰንበት ት/ቤት በማደጌና በግቢ ጉባኤ አገልግሎት በመሳተፌ ባገኘሁት ቃለ እግዚአብሔር መሪነት የወጣትነት ዕድሜ የሚያመጣቸውን ፈተናዎች በቤተ ክርስቲያን ጥላ ሥር ሆኜ እንዳሳልፍ ረድቶኛል። ወጣቶችም እንዲሁ ቤተ ክርስቲያንን ምርኩዝ፣ መጠለያ ናትና ራሳቸውን ወደ መንፈሳዊ ሕይወት ቀስ በቀስ እያሳደጉ በቤተ ክርስቲያን ጥላ ተጠልለው የዓለሙን ሁሉ ፈተና እንዲሻገሩ እመክራለሁ።

በተለይ ለመንፈሳዊ ሕይወታችን ጥንካሬ የሚያግዘን ቦታ የትኛው ነው? መዋል ያለብን በየት ነው? የሚለውን በመለየት መልካምና ተስማሚ አካባቢ መምረጥ ይገባል። እኛም በአለንበት የሥራ ዘርፍ ወጣቱን አድርጉ ከማለት የዘለለ ወጣትነት እግዚአብሔር የሚጠቀምበት ዘመን ስለሆነ ማገዝ ይኖርብናል።

**መጽሔተ ተልእኮ፦** ከአገልግሎት በተለያየ ምክንያት የሚጠፉ ኦርቶዶክሳውያንን ወደ አገልግሎት ለመመለስ ምን መደረግ አለበት ይላሉ?

**ዶ/ር ወሰን፦** ሰዎች ከአገልግሎት በተለያየ ምክንያት ሊጠፉ ይችላሉ። በሥራ ጫና ወይም በግል በሚገጥማቸው በተለያዩ የሕይወት ውጣ ውረዶች ከአገልግሎት ሊርቁ ይችላሉ። አንዳንድ ሰዎች ደግሞ በመድረክ ከሚታየው አገልግሎት የራቁ ቢሆንም በሥራ ቦታቸው፣ በቤተ ሰባቸው ወይም በአካባቢያቸው ክርስቲያናዊ በሆነ መንገድ ሕይወታቸውን የሚመሩ ከሆነ እና በቤተ ሰብ ወይም በሥራ የተጣለባቸውን ኃላፊነት በአግባቡ መወጣት ከቻሉ ክርስቲያናዊ አገልግሎቱን ባሉበት ይዘውት ሄደዋል ማለት እንችላለን።

የማኅበረ ቅዱሳን አገልግሎት በረከት የምናገኝበት አገልግሎታችን ነው። እግዚአብሔር በዘመን ሁሉ የሚፈልገን እንጅ በአንድ ዘመን ብቻ የማፈልገን ስለአይደለ ልጄ ሆይ ወዴት ነህ ሲለን እንሆኝ ልለን ይገባናል። ዛሬም እግዚአብሔር እንድናገለግለው ይጠራናልና እሽ እንበለው። ዘወትር እኛን ሊባርከን ይሻልናል በተሰጠን የአገልግሎት መስክ ከትናንት ይልቅ ዛሬ እንበርታ።

«መልካሙን ሥራችሁን አይተው በሰማያት ያለውን አባታችሁን ያከብሩ ዘንድ ብርሃናችሁ እንዲሁ በሰው ፊት ይብራ፡፡» ማቴ 5÷13-16 የሚል ወንጌልን የምትሰብክ ቤተ ክርስቲያንም ዓለምን ፍጹም በሆነ ክርስቲያናዊ ሕይወታቸው ዋጅተው ሰላምን፣ ፍቅርን፣ ታማኝነትን፣ እውነትን ትጋትን በሕይወታቸው በሚሰብኩ ልጆቿ ደስተኛ ናት፡፡ ነገር ግን በተለያዩ የሕይወት መሰናክሎች ምክንያት በመንፈሳዊ አገልግሎት ሲሳተፉ ቆይተው የመንፈሳዊ ሕይወት ዝለት አጋጥሟቸው በፈተና ውስጥ ያሉ ኦርቶዶክሳውያንን በአገልግሎት ያለን እህቶችና ወንድሞች በተለየ ትኩረትና እንክብካቤ ወደ መንፈሳዊ ሕይወት እንዲመጡ ልናበረታታቸው ይገባናል፡፡

በማኅበሩ ያለፋችሁ ወንድሞቼ እኅቶቼ የእግዚአብሔር ጥሪ እንደ ማይቋረጥ ሁሉ ማኅበራችንም እግዚአብሔርን የምናገኝበት ስለሆነ ከትናንት ይልቅ ዛሬ ልናገለግለው፣ እንሆኝ ልንለው ይገባል፡፡ ማኅበሩ የሰጠንን ተልእኮ በሕይወት ዘመናችን ሁሉ በእውነትና በሀቅ መፈፀም ይኖርብናል፡፡ ይኸውም በቤተ ክርስቲያንም በሀገር ግንባታም ማገልገል መቻል ይኖርብናል፡፡ ማኅበረ ቅዱሳን የሕይወት ዘመን አገልግሎታችን ነው እና መመለስ ይኖርብናል፡፡

**መጽሔተ ተልእኮ፡-** በመጨረሻም የሚያስተላልፉት መልእክት ምንድን ነው?

ዶ/ር ወሰን፡- በአገራችን እንዲሁም በዓለሙ ሁሉ የሚያስጨንቁ ብዙ ነገሮችን እንሰማለን፡፡ ስለዚህ ክርስቲያኖች በሙሉ የጌታችን ክብሩና ኃይሉ የሚገለጽ በመሆኑ፣ ክብሩ በሚገለጥበት ወቅት ከቅዱሳን ጎን ለመቆም ያበቃን ዘንድ በጸሎት እየተጋንና በፍቅር እየተሳሰብን፣ በሃይማኖታችን ጸንተን፣ በትጋት እግዚአብሔርን እንድናገለግለው በሥራ እንድንሠማራ እላለሁ፡፡

## 5. ግብረ ማኅበረ ቅዱሳን

**"ለአገልግሎት እንተጋለን!"**

በ፴፪ኛው አጠቃላይ ዓለም አቀፍ የሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ላይ ጉልህ ድርሻ ከነበራቸው ባለ ድርሻ አካላት አንዱ ማኅበረ ቅዱሳን ነው። ፴፪ኛው አጠቃላይ ዓለም አቀፍ የሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ከእስካሁኑ የተሻለ እንደ ነበር በብዙ መልኩ ሲገለጽ ሰንብቷል። የተሻለ ያስባሉት ጉዳዮችም በመላ ሀገሪቱ ያለው ነባራዊ ሁኔታ ከግምት ውስጥ ገብቶ ነው፡፡

ሀገሪቱ በተለይ ለዓመታት የጦርነት ቀጠና ሆነው የኖሩትን አሁንም በጦርነት ላይ የሚገኙት የሰሜኑ የሀገራችን ክፍሎች በጠና ታመው የባጁበት፣ አብያተ ክርስቲያናት በመልከ ብዙ መከራ ውስጥ የቆዩበትና አሁንም ከችግሩ ያልተላቀቁበት፣ የደቡቡና የምዕራቡ የሀገራችን ክፍሎችም ቢሆኑ ለምእመናን የሞት ምድር ሆነው የቆዩበት አሁንም ችግሩ ያልተፈታበት፣ ሲኖዶሳዊ አንድነትን ለማፍረስና መለካውያንና ሲሞናውያን መንበሩን ለመቆጣጠር ጥረት ያደረጉበት ወቅት በመሆኑ፣ በጥቅሉ የውጭም የውስጥም ጠላቶች ቅድስት ቤተ ክርስቲያንን ለማፍረስ ረፍት ያጡበት ወቅት ስለ ነበረና በዚህ ሁሉ መከራ ውስጥ ሆነውና ይህን ሁሉ ችግር ተጋፍጠው የቤተ ክርስቲያንን ሃይማኖታዊ ተልእኮ ለማስፈጸም ጥረት ያደረጉ ባለ ድርሻ አካላት የታዩበት መሆኑ ነው፡፡

ይህ ብቻ ሳይሆን የጉባኤው ተሳታፊዎችም ሆኑ የቅዱስ ሲኖዶሱ አባላት ቅዱስ ፓትርያርኩን ጨምሮ በግልጽነትና በፍትሐዊነት ተሳትፎ ያደረጉበት፣ የቅድስት ቤተ ክርስቲያንን ወቅታዊ ችግሮች ነቅሶ አውጥቶ የተወያየበት፣ ጉባኤውን የመሩና ያስተባበሩ አባቶችም በተሻለ አቅምና ዝግጅት ጉባኤውን መምራት የቻሉት ወዘተ በመሆኑ በበጎ የተመዘገበ ሆኖ አልፏል፡፡ እንደ ቤተ ክርስቲያን ልጅነት ደስ ያለንና በበጎ የተመለከትነው ተግባር ለመሆኑ ጥርጥር የለውም። በዚህ ጉባኤ በልዩ ልዩ ጉዳዮች ሥራ የሠሩና ጥሩ አፈጻጸም ያሳዩ ሀገረ ስብከቶችና አካላት ታይተዋል፡፡ በጉባኤው ከቀረቡት ተግባራት ማኅበረ ቅዱሳን ያከናወናቸውን ዘርፈ ብዙ አገልግሎት የሚያስመሰግን በወፍ በረር ልናጋራችሁ ወደድን።

ማኅበረ ቅዱሳን ቅድስት ቤተ ክርስቲያን በፕሮቴስታንታዊ ምንፍቅና፣ በአክራሪ እስልምና፣ በኮሚንስታዊ እግዚአብሔር የለሽ ፍልስፍና ዙሪያዋን ተከባ በነበረችበት ወቅት፣ ኦርቶዶክሳዊ ትውልድ እንዳይተካ ይተጉ የነበሩ የቤተ ክርስቲያን ታሪካዊ ጠላቶች በውስብስብ የምንፍቅና ሴራቸው በዙዎችን ኦርቶዶክሳዊያን ከቅድስት ቤተ ክርስቲያን እያወኩ ከምእመናን ኅብረት እየለዩ የምንፍቅናን ካባ ያለበሱ በነበሩበት ወቅት ስብከተ ወንጌል በማስፋፋት ለብዙዎች ቃለ እግዚአብሔርን ያስተማረና ከጥፋት የተዳገ ነው፡፡እንዲያው የ30 ዓመት ሥራዎቹን ለመዘረዝር አቅምና ጊዜው ባይፈቅድም ሩቅ ሳንሄድ በዚህ በ፴፪ኛው አጠቃላይ ዓለም አቀፍ የሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ላይ ከቀረቡት ሥራዎቹ ጥቂቶቹን እናጋራችሁ።

## 5.1 በትምህርተ ሃይማኖትን አገልግሎት፡-

ወጣቱን ትውልድ በተለይ ዘመናዊ ትምህርት ተብሎ ምዕራባዊነትንና የሴኩላሪዝም መርዝ የተጋተውን፣ ሃይማኖተኝነትን እንደ ኋላ ቀርነት የሚቆጥረውን፣ ኢትዮጵያ ተቀምጦ አውሮፓንና አሜሪካን በምናቡ ሲቀላውጥ የሚውለውን፣ ለፍልስፍና፣ ለክሕደት፣ ለዘመናዊነት እንደ ወረርሽኝ በፍጥነት የሚተላለፍ ለባዕዳን ባህል እንዲሁም ለዓይነተ ብዙ ሱስ ተጠቂነት ቅርብ የሆነውን ወጣት ታሳቢ ያደረገ ተተኪነትን ግምት ውስጥ በማስገባት፣ የትውልዱን ተግዳሮት ተረድቶ የሚሠራ ተቋምም ማኅበርም ብዙ አልታየም፡፡ ማኅበሩ ባለፉት ዓመታት ከ800,000 የሚልቁ ወጣቶችን አስተምሮ ፈጣሪያቸውን አማኝ፣ ለሀገራቸው ታማኝ የሆኑ በግብረ ገብነት እንዲሁም በሀገርና ሕዝብ ወዳድነት የሚታወቁ፣ በአቋራጭ ለመክበር፣ ባልደከሙበት ለመበልጸግ፣ ሀገር የማይዘርፉ፣ ሁለገብ አገልጋዮችን ማፍራቱ የአደባባይ እውነት ነው፡፡

ማኅበሩ በዚህ ሰዓት በ467 የሀገር ውስጥ እና በ18 የውጭ ሀገር ግቢ ጉባኤያት ውስጥ በተለያዩ ቋንቋዎች ከ300,000 በላይ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተማሪዎችን እያስተማረ ይገኛል። በዚህ ባለንበት ወቅት ለጵጵስና ሹመት ለደብር አለቅነት የሚሻኮቱ የቤተ ክርስቲያንን አገልጋዮች እያየየን እየሰማን ነው፡፡ አሁን በዚህ ሰዓት የደብር አለቃ ለመሆን፣ ጳሓፊ፣ ቁጥጥር ወይም ቄስና ዲያቆን ሆኖ በታላላቅ አድባራት ለመቀጠር ብድርና ቁጠባ ተበድሮ ወይም ቤት ሸጦና አሻሽጦ ወይም ከገጠር መሬቱን በአራጣ አስይዞ ጉቦ የሚከፍል አገሊጋይ ብዙ ነው፡፡ ነገር ግን ገጠሩ ተፈትቷል፤ ጉባኤው ታጥፏል፤ መምህራኑም እያስተማሩ አይደሉም፤ ተማሪዎቹም ከጉባኤ ቤቶች የሉም፤ ምክንያቱም ከበዓታቸው ወጥተው ከተማ ከገቡ ቆይተዋል፡፡ የነገው ጳጳስ፣ የነገው ቄስና ዲያቆን፣ መርጌታና መነኮሴ ከየት ይመጣ ይሆን ብሎ እየተጨነቀ ያለ አካል ግን ብዙ አይታይም፡፡

ማኅበረ ቅዱሳን ግን ነገን አስቦ ተጨንቋል፡፡ መጻኢው ዘመን አሳስቦታል፡፡ ጉባኤው እንዳይፈታ፣ ወንበሩ እንዳይታጠፍ፣ አብነቱ ያለአብነት እንዳይቀርና ገዳማቱ ታሪክ ሆነው እንዳይቀሩ ከሚያደርገው ጥረት ባሻገር ለመጻኢው ችግር ሌሎች የመፍትሔ አማራጮች በመጠቀም በ35 ማእከላት 7966 የግቢ ጉባኤ ተማሪዎችን ከኮርስ ትምህርታቸው ጎን ለጎን የአብነት ትምህርት እያስተማረ ይገኛል፡፡ በዚህ ዓመት ብቻ ከእነዚህ መካከል ለክህነት የደረሱ 195 ተማሪዎችን ክህነት እንዲቀበሉ አድርጓል፡፡

## 5.2 ስብከተ ወንጌልን በተመለከተ፡-

በቤተ ክርስቲያን ታሪክ እንደተማርነው ከግራኝ አሕመድ ወረራ በኋላ የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ከደቡብ ወደ ሰሜን ከገጠር ወደ ከተማ ተሰብስቦ በመቅረቱ፣ ወንጌልን በየቋንቋቸው ልናደርስላቸው ባለመቻላችን በርካታ ምእመናን ከቤተ ክርስቲያን ርቀው ለሌላ እምነት ተቋም ሲሳይ ሆነው መቅረታቸው ግልጽ ነው፡፡ ቤተ ክርስቲያን ትልቁ ተልእኮዋ ወንጌለ መንግሥትን መስበክ ያላመኑትን ማሳመን፣ ያመኑትን ማጽናት፣ የጸኑትን ለክብር ለመንግሥተ ሰማያት እንዲበቁ በማድረግ ነውና ማኅበረ ቅዱሳን ስብከተ ወንጌልን ለማስፋፋት ብዙ ደክሟል፤ ዓለምን ዞሯል፤ ገጠር ከተማውን፣ ቆላ ደጋውን አዳርሷል፡፡ ለበርካታ ነፍሳትም ልጅነትን አሰጥቷል፤ በመከራ ውስጥ ላሉትም የመጽናኛውን ወንጌል አድርሶላቸዋል፤ በዚህ ዓመትም በተለያዩ ቋንቋዎች በስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ አገልግሎት ለሚሰማሩ አገሊጋዮች

- ለ865 ሰባክያነ ወንጌል፣
- ለ218 የጎሣ መሪዎች ፣
- ለ231 ባለሙያዎች፣
- ለ130 በውጭ ሀገር ለሚሰማሩ  አገልጋዮች፣
- ለ1983 ካህናት አባቶችን በስብከተ ወንጌል ለማሰማራት  በክብረ ክህነት እና መምህረ ንስሓነት ሥልጠና ሰጥቷል፡፡

በዚህ ዓመት ብቻ ስብከተ ወንጌልን ለማስፋፋት ባከናወናቸው ተግባራት

- ለካህናት ሥልጠና ........ 3,807,749.00 ብር፤
- ለ204 ሰባክያነ ወንጌል ወርኃዊ ደመወዝ ..... 3,152,400.00 ብር፤
- በተለያዩ ቋንቋዎች ለተደረጉ 188 ትምህርታዊ ጉባኤያት ማስፈጸሚያ ................. 3,760,000.00 ብር ፤
- በ14 የተለያዩ  ቋንቋዎች ትምህርቶችን ለሚያዘጋጁ፣ ለሚተርጎሙና የአርትኦት ሥራ ለሚሠሩ  32 አገልጋዮች ሥልጠና 265,000.00 ብር ፤
- 36,635 አዳዲስ አማንያን በሀገር ውስጥና እና 48 አዳዲስ አማንያን ደግሞ በውጭ ሀገር አስተምሮ ለማስጠመቅ ........................ 4,501,144.00 ብር ፤
- 231 የአዳዲስ አማንያንን ልጆችን የአብነት ትምህርት ባሉበት እና ዘጠኝ ልጆች ደግሞ  በፍኖተ ሰላም አቡነ ቶማስ መታሰቢያ ቤተ ጉባኤ በመማር ላይ ላሉ 277,748.00 ብር ወጭ አውጥቷል፡፡

የእግዚአብሔር ቤተ ሰቦች ማኅበረ ቅዱሳን ለስብከተ ወንጌል ምን ያክል ትኩረት እንደሰጠ አስተዋላችሁ?  ይህ ብቻ አይደለም፤ ሌላም አለ። ለአዳዲስ አማንያን በተለያዩ ጠረፋማ አካባቢዎች 13 አቢያተ ክርስቲያናትን እያሠራ ሲሆን ሰባቱን አስመርቆ ለአገልግሎት አብቅቷል። ሁለቱ ተጠናቀው ቅዳሴ ቤታቸውን በማክበር ዝግጁ ሆነዋል። ለዚህ አገልግሎትም 27,790,019.00 ብር ወጪ አድርጓል፡፡

ለ2,363 ተማሪዎች በደረጃ አንድ እና የደረጃ ሁለት አመራር (የመሪነት) ሥልጠና ሰጥቷል፤ የውጭ ዜጎችን፣ ኢትዮጵያውያንና ዲዮስፖራዎችን መሠረት ያደረጉ አራት ቨርቹዋል ግቢ ጉባኤያትን አቋቁሟል፤ ለዓይነ ሥውራን የሚሆኑ ሁለት የግቢ ጉባኤያት የኮርስ መጻሕፍት በድምጽ አዘጋጅቷል፡፡

5 የግቢ ጉባኤያት የኮርስ መጻሕፍት በአማርኛና በኦሮምኛ ቋንቋዎች በድጋሜ አሳትሟል፤ ለአዳዲስ አማንያን ቅድመ እና ድኅረ ጥምቀት ማስተማሪያ የሚሆኑ አምስት (5) የስብከት ኬላ አዳራሾች በ 4,120,888.00 ብር ወጪ አሠርቷል፡፡

በተጨማሪም ስብከተ ወንጌልን በተለያየ የአገልግሎት አማራጮች ተደራሽ ለማድረግ በርቀት ትምህርት 1155፣ በጥራዝ ትምህርት (ሞጁል) እና በትምህርት ማሠራጫ ድረ ገጽ (ኢ- ለርኒግ) ለዘጠና አንድ (91) ተማሪዎች የቅድስት ቤተ ክርስቲያንን መሠረተ እምነት ለማስተማር .... 652,232.00 ብር ወጪ አድርጓል፡፡ ምክንያቱም ይህ ሁሉ ስለወንጌል የተደረገ ነውና፡፡

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ **"በወንጌልም ማኅበርተኛ እሆን ዘንድ ስለ ወንጌል ሁሉን አደርጋለሁ"** (፩ኛ ቆሮ ፱፡፳፫) እንዳለ ሳይተርፋቸው የሚሰጡ፣ እየደከማቸው የማይታክቱ፣ ብርቱዎች ለቤተ ክርስቲያን በጎደለው የሚሞሉ በፈረሰው የሚቆሙ ቅጥር ጠባቂዎች አባላት ያሉት ማኅበር በሁሉ ያሉ፣ ለሁሉ የሆኑ፣ በቤተ ክርስቲያን ጉዳይ የማያንቀላፉ፣ ትጉሆች፣ የማይረቱ ታጋዮች፣ በጥቅም የማይገመቱ ለክብሯ ቀናተኞች፣ በሁሉ የተከበሩና የታፈሩ አልፎም የሚፈሩ አባላት ሺህ ሆነው እንደ አንድ ጥቂት ሆነው እንደ ሽህ የሚሠሩ ናቸው፡፡

## 5.3 በሙያና ማኅበራዊ አገልግሎትን፡-

ማኅበረ ቅዱሳን ብዙ ሀገራዊና ሃይማኖታዊ ሸክሞችን ተሸክሟል። በድርቅ የተጎዱ፣ በግጭት የተፈናቀሉ ከተማቸው የወደመባቸው፣ ቤታቸው የተቃጠለባቸው፣ ሀብት ንብረታቸው የተዘረፈባቸው፣ የእምነት ተቋማቸው የፈረሰባቸው፣ በሃይማኖታቸው ምክንያት መከራ ዘወትር የሚገበኛቸው፣ ሰማዕት በደም እና ሰማዕት ዘእንበለ ደም የሆኑ ሁሉ በአራቱ ማዕዘናተ ኢትዮጵያ በመከራ ያሉ ሁሉ የማኅበረ ቅዱሳንን በር ያንኳኳሉ፡፡ ከዚህም የተነሣ አንዱን ክፍተት ሲሞላ ሌላ ክፍተት ይፈጠራል፤አንዱን እሳት ሲያጠፋ ሌላ እሳት በሌላ ቦታ ይለኮሳል፤ በዚህም ምንም ዓይነት ሃይማኖታዊ ልዩነት ሳያደረግ በመከራ ውስጥ ያሉትን ኢትዮጵያውያን ሁሉ በአረፉበት በየተጠለሉበት አካባቢ እየተገኘ ማኅበሩ ማኅበራዊ ኃላፊነቱን ለመወጣት ያደረገው ጥረትና ያስገኘው ውጤት ደግሞ ከክርስትና ሃይማኖት ውጭ ያሉትን የእምነት ተከታዮች ሳይቀር በእጅጉ የሚያስደሰት ነው፡፡

ማኅበራዊ አስተዋጽኦውን ስንመለከት በአራት ሀገረ ስብከቶች ማለትም በሰሜን ምዕራብ ሸዋ /ሰላሌ ፍቼ፣ በምዕራብ ሸዋ አምቦ፣ ሰሜን ሸዋ አጣየና ሸዋሮቢት፣ እንዲሁም ዋግኽምራ ለሚገኙ 1015 ተማሪዎች 809,395.00 ብር በላይ ወጪ የሆነበት የትምህርት ቁሳቁስ ድጋፍ አድርጓል። ለሻሸመኔ የሰማዕታት ቤተ ሰቦችና በአዲስ አበባ ወለቴ ለሚገኙ ተጎጂዎች በድምሩ 353,000.00 ብር የሕክምና ድጋፎች አድርጓል፣ በጦርነቱ ለተጎዱ 10 የትግራይ ገዳማት መነኮሳት፣ አብነት ተማሪዎችና አገልጋዮች 820,000.00 የፈጀ አስቸኳይ ድጋፍ አድርጓል።

ለቦረና ተጎጂዎች 397,100.00 ብር፣ በጎንደር አዘዞ ቀበሮ ሜዳ ጊዜያዊ መጠለያ ጣቢያ ለሚገኙ ተፈናቃዮች ከ500,000.00 በላይ ወጭ ተደርጎ አስቸኳይ የምግብ ግብዓቶች ድጋፍ፣ በሃይማኖት ጥቃትና መፈናቀል የከፋ ችግር ለደረሰባቸ ካህናትና አገልጋዮች የ 266,675.00 ብር ድጋፍ ያደረገ ሲሆን በአጠቃላይ ለአስቸኳይ የማኅበራዊ ድጋፍ ፕሮጀክቶች ትግበራ 3,448,045.00 በላይ ወጪ ተደርጓል።

ይህ ብቻ አይደለም ማኅበረ ቅዱሳንን እጅግ ልዩ ከሚያደርጉት ነገሮች አንዱ የአባላቱ የሙያ ስብጥር ነው። እነዚህ የልዩ ልዩ ሙያ ባለቤት አባላቱ ከገንዘባቸው እና ከዕውቀታቸው እንዲሁም ከጊዜያቸው በተጨማሪ የሙያ አገልግሎት የሚሠጡ ናቸው፡፡ ነፃ የሕግ፣ የሕክምና፣ የምሕንድስና፣ የሥልጠና እና ሌሎችንም የሙያ አገልግሎት ለቤተ ክርስቲያናቸው ይሰጣሉ። በዚህ ዓመት ብቻ ሙያዊ ግምታቸው 9,710,600.00 የሆኑ 42 ልዩ ልዩ ይዘት ያላቸው የቤተ ክርስቲያን እና ልዩ ልዩ የአገልግሎት ሕንፃ ዲዛይኖችን እና 2.3 ሚሊዮን ብር የሆኑ የገቢ ማስገኛ ፕሮጀክቶች በነጻ ሠርተው አበርክተዋል፡፡

በተጨማሪም 4.5 ሚሊዮን የገንዘብ ግምት ያላቸው 20 የሚሆኑ የምሕንድስና መስክ ሱፐርቪዥን አገልግሎቶች ተሰጥተዋል። በዚህ እንደ መርፌ ቀዳዳ በጠበበ ዘመን፣ የሰው ልጅ ኑሮን ለማሸነፍ ረፍት ባጣበት ወቅት፣ ራስ ወዳድነትና ፍቅረ ንዋይ ዓለሙን በገዛበት፣ ትውልዱ በሥጋ ፍላጎቱ በሚናውዝበት በዚህ በእኛ ዘመን መላ ነገርን ለቤተ ክርስቲያን መስጠት እንዴትስ ይቻላል? በገፊዎች ዘመንስ ከግፉዓን ወገን መቆም እንዴት ያለ መልካምነት ነው? ሳይተርፍ መስጠትስ ምን ዓይነት ልግስና ነው? ራስን ጎድቶ ሌላውን መጥቀምስ ለስንቶች ይቻላል? ብቻ ወንድሞቻችን የጨለማ ዘመን መቅረዞቻችን ናችሁና እግዚአብሔር በዕድሜና በጤና ይጠብቃችሁ፤ አገልግሎታችሁንም ይባርክላችሁ እንላለን!

## 5.4 በቅዱሳት መካናትና መንፈሳዊ ትምህርት ቤቶች አገልግሎት፡-

ማኅበሩን ከሚያስደንቀው ተግባሩ አንዱ በቅዱሳት መካናትና አብነት ትምህርት ቤቶች ላይ የሚሠራው ሥራ ነው፡፡ ከላይ እንደተገለጸው ዛሬ ላይ ሆኖ ነገ የሚያስጨንቀው የተተኪ የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት አገልጋዮች ጉዳይ መሆኑና ተተኪ ለማፍራት ገዳማቱ አብነት ትምህርት ቤቶቹ እንዳይነጥፉ አበክሮ የሚሠራ መሆኑ ነው። ከዚህም የተነሣ ማኅበረ ቅዱሳን ሩቅ አላሚና ነገን ዛሬ ላይ እየሠራ ያለ ዓለም አቀፍ ተቋም ነው።

በቅዱሳት መካናት እና አብነቱ ረገድ በዚህ ዓመት ያከናወናቸው ተግባራት በጉባኤው የቀረቡ ሲሆን በዚህም ለ229 የጉባኤ ቤት መምህራን እና ለ1949 ደቀ መዛሙርት ድጎማ 5,544,500.00 ብር ለ103 የአባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ ነፃ የትምህርት ዕድል ተጠቃሚዎች 1,271,600.00፣ ከደቡብ፣ ከምዕራብ እና ከምሥራቅ ከሚገኙና የአገልጋዮች እጥረት ካለባቸው አካባቢዎች ለተውጣጡ 83 ዲያቆናት ተጨማሪ የአብነት ትምህርት እንዲማሩ 448,200.00 ብር፣ በጦርነት ለተጎዱ በሰሜን ወሎ እና በዋግኽምራ ለሚገኙ 12 ገዳማት እና 13 የአብነት ትምህርት ቤቶች እንዲሁም ለጣና ቂርቆስ አራቱ የመጻሕፍት ጉባኤ አዳሪ የአብነት ትምህርት ቤት 1,610,000.00 ብር የቀለብ ድጋፍ፣ በሶማሌ፣ በአፋር፣ በአርሲ አህጉረ ስብከት በ15,518,741.84 ብር በማስገንባት አብነት ትምህርት ቤቶችን ለሀገረ ስብከቶቹ አስረክቧል።

እንዲሁም በእንጦጦ ሐመረ ኖኅ ቅድስት ኪዳነ ምሕረት ገዳም አብነት ትምህርት ቤትና የመምህራን ማረፊያ ቤት ግንባታ ፕሮጀክት በብር 1,236,386.53 ወጪ የተጠናቀቀው በዚህ ዓመት በዚሁ ማኅበር ነው፡፡ ማኅበሩ የአከናወናቸው ተግባራት እነዚህ ብቻ አይደሉም በልዩ ልዩ ቋንቋዎች የመዝሙር ሲዲዎችን አሳትሟል፤ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንን ሀገራዊና ዓለማቀፋዊ ሚና የሚያሳዩ በርካታ የጥናት ጉባኤዎችን አድርጓል፤ በጥናት መጽሔት ያሰራጫል፤ በስድስት የሀገር ውስጥና በአንድ የውጭ ሀገር ቋንቋ በቴሌቪዥን ተመራጭና የቤተ ክርስቲያን ድምጽ ለመሆን ችሏል፤ "ቅዱስ ያሬድና ሥራዎቹን የሚዘክሩ መዝሙሮችንና ዐውደ ርእይ አሳይቷል፡፡

የተወደዳችሁ አንባብያት! እንግዲህ እነዚህ በዝርዝር ያቀረብናችሁ ከማኅበሩ ሥራዎች ጥቂቶቹ ናቸው፡፡ እነዚህ የቀረቡት ያለፉትን 30 ዓመታት ሥራዎቹንም አይጨምሩም፡፡ እነዚህ ያያችኋቸው ሥራዎች ሀገራችንም ሆነ ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን እንደ ብራና ተወጥረው በከረሙበት፣ በብዙ ሰቆቃና ለቅሶ በጦርነትና በመከራ ባሰለፍንበት ባለፈው 2015 ዓም ብቻ የተከናወኑ ናቸው፡፡ በዚህ ድንቅ ተግባር በእሳት ላይ ቆሞ በእሳት ላይ እየተረማመዱ ይህን ያክል መሥራት ከተቻለ ሀገራችንና ቤተ ክርስቲያናችን ሰላም በሆኑ ደግሞ ምን ያህል ሥራ መሠራት እንደሚቻል መገመት አያዳግትም፡፡ የቤተ ክርስቲያናችን ትንሣኤ በቅርቡ እውን እንደሚሆን አንጠራጠርም፡፡ ይህ ሁሉ በአንድ ማኅበር ብቻ የተሠራ ነው፡፡ ብዙ ማኅበራት አሉን፤ ብዙ አህጉረ ስብከት አሉን፤ ብዙ ምእመናንም አሉን፤ ሁሉም የድርሻውን ሲወጣ ሁሉም ይሆናል፡፡

የተወዳጆችሁ የእግዚአብሔር ቤተ ሰቦች! ታዲያ ለዚህ በዓላማው ለጸና፣ አደራውን ለማያጎድል፣ ሥርቶ ለሚያሳይ፣ የሰማይ ቤታችንን ሊሠራልን የሚተጋ፣ የቤተ ክርስቲያናችን የሃይማኖታችን ዘብ፣ የጠላቶቻችን መዶሻ የሆነ የልጆቻችንን ነገ ዛሬ ለሚያበጅልን ማኅበር "ማኅበረ ቅዱሳን" አጋርነታችን እስከምን ድረስ ነው?

"አባቶቻችን ሆይ በመንፈስ ቅዱስ መሪነት መልካሙን ገድል የሚጋደል ማኅበር
ለትውልዱ አትርፋችኋልና እናመሰግናችኋለን" !!!

# 6. ይናገራል ፎቶው



ማኅበረ ቅዱሳን በ1998 የዋና ማእከል



ከገንዘብ መዋጮ ባለፈ አባላት በዕውቀታቸው እና በጉልበታቸው ድጋፍ አድርገዋል



ባለ ሰባት ወለል ሕንጻ ለመገንባት አባላት የወር ደሞዛቸውን እንዲያዋጡ ተደርጓል



# 7. ማኅበረ ቅዱሳን በማእከላት

## የአዲስ አበባ ማእከል አገልግሎት እንቅስቃሴ

### አዲስ አበባ ማእከል

ማኅበረ ቅዱሳን በሀገር ውስጥ ካደራጀቸው 52 ማእከላት ውስጥ አዲስ አበባ ማእከል አንዱ እና ዋነኛው ማእከል ነው፡፡ ማእከሉ በ1986 ዓ/ም የተቋቋመ ሲሆን በአሁኑ ሰዓት በሥሩ 9 ወረዳ ማእከላት/ ሰንዳፋን እና ለገጣፎን ጨምሮ/፣ ከ 67 በላይ ግቢ ጉባኤያት፣ከ20 በላይ መደበኛ አባላት፣ከ5500 በላይ ኢ-መደበኛ አባላት እና ተባባሪ አባላት እና 37 ሠራተኛ ጉባኤ በመያዝ ዘርፈ ብዙ አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል፡፡

የማእከሉ ግንባር ቀደም አገልግሎት የከፍተኛ ተቋማት ተማሪዎች ትምህርተ ሃይማኖት እና ሥርዓት ቤተ ክርስቲያንን በማስተማር በዕውቀት የበለጸገ እና በሥነ ምግባር የታነጸ ብቁ ዜጋ በማፍራት ለቤተ ክርስቲያን እና ለሀገር ተተኪ ማፍራት ሲሆን፣በተጨማሪም የስብከተ ወንጌል እና ሐዋርያዊ አገልግሎት በማስፋፋት፣ አባላትን በማሰማራት እና ፕሮጀክቶችን በመቅረጽ የገዳማት፣ የአጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት እና የሰ/ት/ቤቶችን አገልግሎት በመደገፍ እና ምእመናን ቤተ ክርስቲያናቸውን አውቀው እንዲጠበቁ እና እንዲያገለግሉ በማድረግ አርአያነት ያለውን አገልግሎት እየሰጠ የሚገኝ ማእከል ነው፡፡

### አዲስ አበባ ማእከል ያከናወናቸው ዐበይት ተግባራት በከፊል

- በከፍተኛ ተቋማት የሚገኙ ኦርቶዶክሳዊ ወጣቶችን በማስተማር ባለ ተልእኮ ማድረግ
- ስብከተ ወንጌል እና ሐዋርያዊ አገልግሎትን ማስፋፋት
- ገዳማትን በመደገፍና አብነት ት/ት ቤቶችን ማጠናከር እና ማስፋፋት
- የሙያ እና ማኅበራዊ አገልግሎት መስጠት
- የመዝሙር እና የኪነ ጥበብ አገልግሎት

### ❖ በከፍተኛ ተቋማት የሚገኙ ኦርቶዶክሳዊ ወጣቶችን በማስተማር

ማኅበረ ቅዱሳን ከተቋቋመበት ዐበይት ዓላማዎች ዋነኛው በከፍተኛ ተቋማት የሚገኙ ተማሪዎችን በማስተማር ለሀገር እና ለቤተ ክርስቲ ያን ተተኪ ትውልድ ማፍራት ነው፡፡ ማእከላችን ዋና ተቀዳሚ አገልግሎቱ የግቢ ጉባኤ አገልግሎት ሲሆን በአሁኑ ሰዓት ከ 67 በላይ ግቢ ጉባኤያትን በማቀፍ በተዘጋጀው ሥርዓተ ትምህርት በማስተማር፣ በማሠልጠን እና የቤተ ክርስቲያንን አገልግሎት እንዲለማመዱ በማድረግ በአባቶች ቡራኬ በማስመረቅ ባለተልዕኮ በማድረግ እያሠማራ ይገኛል፡፡

ማእከሉ በአሁኑ ሰዓት ከ12 ሺ በላይ ተማሪዎችን በመንግሥት እና በግል ከፍተኛ ተቋማት የሚገኙ ተማሪዎችን አቅፎ የሚያስተምር ሲሆን ከ17 በላይ ኮንትራንት መምህራን እና ከ20 በላይ በጎ ፍቃደኛ መምህራንን በመመደብ በሳምንት 246 የኮርስ ጉባኤያትን እያካሄደ ይገኛል፡፡ ማእከሉ ላለፉት 28 ዓመታት ከ50ሺ በላይ በዕውቀት የበለጸጉ በሥነ ምግባር የታነጹ ተማሪዎችን በማስተማር ለአገልግሎት አሰማርቷል፡፡

አብዛኞቹ በተለያዩ የቤተ ክርስቲያን መዋቅራት ውስጥ እና በማኅበሩ አገልግሎት ሥር ተሠማርተው ሀገር እና ቤተ ክርስቲያን የጣለችባቸውን አደራ በትጋት እየተወጡ ይገኛሉ፡፡



የተማሪዎች ምርቃት



የተማሪዎች መንፈሳዊ ጉዞ

### ስብከተ ወንጌልን በማስፋፋት እና ሐዋርያዊ አገልግሎት በመስጠት

ማእከሉ በዘጠኙም ወረዳ ማእከላት ባቋቋመው የትምህርት እና ሐዋርያዊ አገልግሎቱ በአ/አ እና በዙሪያዋ በሚገኙ ከ250 በላይ አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት መምህራንን በመመደብ ስበከተ ወንጌል እና ሐዋርያዊ አገልግሎትን በማስፋፋት ላይ ይገኛል፡፡ ማእከሉ ተተኪ ሰባክያንን ፣ ካህናትንና የደብር አስተዳዳሪዎችን ልዩ ልዩ ሥልጠናዎችን በማሠልጠን የስብከተ ወንጌሉ እና የሐዋርያዊ አገልግሎቱ ተግባር እንዲቀላጠፍ እያደረገ ይገኛል፡፡ ማእከሉ እስካሁን ላለፉት 29 ዓመታት ከ3000 በላይ ተተኪ ሰባክያንን በማሠልጠን ወደ አገልግሎት ያሰማራ ሲሆን፣ በተጨማሪም በተለያየ ዙር ከ1500 በላይ ካህናትን ፣ የደብር አስተዳዳሪዎችን፣ የሰ/ት/ቤት አገልጋዮች በማሠልጠን የወንጌል አገልግሎቱ እንዲጠናከር አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡ በተጨማሪም የርቀት ትምህርት በማዘጋጀት በአሁኑ ሰዓት 97 ተማሪዎች ተመዝግበው እየተማሩ ይገኛሉ፡፡



የአ/አ አድባራት እና ገዳማት አስተዳሪዎች ሥልጠና



የካህናት እና የመምህራን ሥልጠና

ማእከሉ ሐዊረ ሕይወት በሚል ታላቅ የምእመናን መንፈሳዊ ጉዞ በማዘጋጀት ላለፉት ሰባት እና ስምንት ዓመታት የስብከተ ወንጌል አገልግሎት በልዩ ሁኔታ ለምእመናን እያደረሰ ይገኛል፡፡






እስከ 10 ሺህ ምእመናን የሚሳተፉበት በዓመት ሁለት ጊዜ የሚዘጋጅ ሐዊረ ሕይወት መርሐ ግብር

በተጨማሪም ከዛሬ 3 ዓመት ጀምሮ በአ/አ እና በዙሪያዋ በሚገኙ ሰንዳፋ እና ለገጣፎ ከተማ ላይ የሚተገበር የፍኖተ ጳውሎስ ፕሮጀክት በመቅረጽ በተለያየ ምክንያት ከእናት ቤተ ክርስቲያን የጠፉትን እና አዳዲስ አማንያንን ወደ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን የመመለስ ሥራ እየተሠራ ይገኛል፡፡ በዚህ መሠረት ፕሮጀክቱ ከተጀመረ ጀምሮ ከ200 በላይ ኢ-አማኒያን ተምረው የሥላሴ ልጅነት እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡



የፍኖተ ጳውሎስ መርሐ ግብር ለምእመናን ሲተዋዋወቅ



ኢ-አማኒያን የሥላሴ ልጅነት ሲያገኙ

### ❖ ገዳማትን በመደገፍና አብነት ት/ት ቤቶችን ማጠናከር እና ማስፋፋት

ማእከሉ ሌላው ከሚሰጣቸው አገልግሎቶች አንዱ ገዳማትን መደገፍ እና የአብነት ት/ት እንዲስፋፋ ማድረግ ነው፡፡ ማእከሉ የአብነት መምህራንን በመቅጠር የግቢ ጉባኤ ተማሪዎችን፣ የሰ/ት/ቤት ወጣቶችን እና ምእመናን የአብነት ትምህርት በመስጠት ላይ ይገኛል፡፡ ማእከሉ በተለያየ ጊዜ ያስተማራቸው ከ350 በላይ ተማሪዎች የአብነት ትምህርት ተምረው ዲቁና ተቀብለው ለአገልግሎት ተሰማርተዋል፡፡ በተጨማሪ በተለያዩ ርእሰ ጉዳይ ለአብነት መምህራን እና ተማሪዎች ሥልጠና ተሰጥቷል፡፡

ማእከሉ በተለያየ ጊዜ በአ/አ እና በአ/አ ዙሪያ ለሚገኙ ገዳማት እና የአብነት ት/ቤቶች ጊዚያዊ እና ዘለቄታዊ ድጋፍ እያደረገ ይገኛል፡፡ የአብነት ት/ቤቱን የበለጠ ለማስፋፋት ቀደም ሲል በሰንዳፍ ከተማ የጀመረው ዘመናዊ የአብነት ት/ቤት ግንባታ ተጠናቆ ግንቦት 13/2015 ዓ.ም የሰሜን ሸዋ ሰላሌ ሀገረ ስብከት ተወካይ በተገኙበት ርክክብ ተደርጓል ፡፡ይህ 5,460,588.91 (አምስት ሚሊዮን አራት መቶ ስድሳ ሺህ አምስት መቶ ሰማኒያ ስምንት ብር ከዘጠና አንድ ሳንቲም) ወጪ የተደረገበት የአብነት ት/ቤት ግንባታ ፕሮጀክት ለ4 መምህራን መኖሪያ የሚሆኑ 4 ክፍሎች፣ 208 ተማሪዎችን ማስተናገድ የሚችሉ 8 ክፍሎች፣ ለልዩልዩ አገልግሎት የሚዉሉ 3 ክፍሎች እንዲሁም 3 መማሪያ ጎጆ ቤቶችን ያካተተ ሲሆን የተገነባው አብነት ት/ቤቱ በወረዳውና በሀገረ ስብከቱ ያለውን የአገልጋይ እጥረት ከመቅረፍና በአካበቢው ቋንቋ አገልጋዮችን ከማፍራት አንጻር ጉልህ አስተዋጽኦ ይኖረዋል ተብሎ ይጠበቃል፡፡



የሰንዳፋ በኬ ደ/ም/ቅ/ ማርያም ዘመናዊ የአብነት ት/ት ቤት የምረቃ መርሐ ግብር

### ◈ የሙያ እና ማኅበራዊ አገልግሎት በማበርከት

ማእከሉ በተጨማሪ ከሚሰጣቸው አገልግሎት ውስጥ ሌላው በሙያ እና በማኅበራዊ አገልግሎት የሚያበረክተው አስተዋጽኦ ነው፡፡ በዚህ ረገድ ቤተ ክርቲያን በሕንጻ ዲዛይን አገልግሎት የምታወጣው በመቶ ሚሊዮን የሚቆጠር ወጪ በነጻ በመስጠት አገልግሎት እየሰጠ ሲሆን ፣ በተጨማሪም ነጻ የጤና አገልግሎት ድጋፍ ለአቅመ ደካሞች በመስጠት፣ የፕሮጀክት አዘገጃጀት፣ የፋይናንስና እና የሰው ሃይል ሥልጠናዎችን በመስጠት እንዲሁም አገልግሎትን የሚያቀላጥፉ ሶፍትዌሮችን በማዘጋጀት ቤተ ክርስቲያን ዘመኑን የዋጀ አገልግልሎት መስጠት የሚያስችላትን አቅም እየፈጠረ ይገኛል፡፡

ማእከሉ ባለድርሻና አጋር አካላትን በማስተባበር በማኅበራዊ ዘርፉ ችግር ለገጠማቸው የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች ካህናት እና የአብነት ተማሪዎች ጊዜያዊ እርዳታ በመስጠት አገልግሎት እያከናወነ ሲሆን፡፡ ከቅርብ ጊዜ ጀምሮ የመግደላዊት ማርያም የሴቶች መንፈሳዊ እና ኢኮኖሚያዊ ፕሮጀክት በሚል በሴተኛ አዳሪነት የሚተዳደሩ እኅቶቻችንን ከዚህ አስከፊ ሕይወት ለማውጣት ፕሮጀክት ቀርጾ ተባባሪ አካላትን በማስተባበር ተግባራዊ በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡ በዚህ መሠረት በዚህ ዓመት የሙከራ ትግበራ የሚከናወንባቸው ሦስት እኅቶች ተለይተው የፕሮጅቱ ተጠቃሚ እንዲሆኑ እየተሠራ ይገኛል፡፡


በምሕንድስና ክፍል የተሠራ ዲዛይን


ለገዳማት እና አብነት ተማሪዎች ጊዚያዊ ድጋፍ

### ◈ መዝሙር እና ሥነ ጥበባት አገልግሎት

ኦርቶዶክሳዊ የመዝሙር ሥርዓት እና የቅዱስ ያሬድ የዜማ ቅኝት ሳይከለስ እና ሳይበረዝ ከትውልድ ወደ ትውልድ እንዲሸጋገር በማድረግ ፣ የቤተ ክርስቲያናችን ልዩ ልዩ መንፈሳዊ ሃብታትን በኪነ ጥበቡ ዘርፍ በማስተዋወቅ አገልግሎት የሚሰጥበት ሌላኛው የአገልግሎት ዘርፉ ነው፡፡ በተለይ በየዓመቱ በአደባባይ የሚከበሩ የመስቀል እና የጥምቀት በዓላትን በልዩ ድምቀት እንዲከበሩ በማድረግ የቅዱስ ያሬድን ዜማ የጠበቁ በልዩ ልዩ ቋንቋ የተዘጋጁ ጥዑመ ዝማሬዎችን በማሰማት አገልግሎት ይሰጣል፡፡

በተጨማሪም ለግቢ ጉባኤያት፣ ለሰ/ት/ቤቶችና እና ለማኅበራት የመዝሙር እና የኪነ ጥበብ ሥልጠናዎችን በመስጠት አገልግሎት እያከናወነ ይገኛል፡፡



የበዓለ መስቀል የዓደባባይ የመዝሙር አገልግሎት



በሐዊረ ሕይወት የመዝሙር አገልግሎት

ማእከሉ ከቅርብ ጊዜ ጀምሮ ግብረ ማኅቶት በሚል መረሐ ግብር ፕሮጅክት በመቅረጽና ለአባላት እና ተባባሪ አካላት በማስተዋወቅ ተግባራዊ እያደረገ ይገኛል፡፡

## ◈ የአዲስ አበባ ማእከል ሕንጻ ፕሮጅክት

ማእከሉ አገልግሎቱን በበለጠ ለማሳደግ እና ለማስፋት አሁን እየተገለገለበት ያለው ከ200 ካሬ ያነሰ አንድ ወለል ጠባብ ቦታ ሲሆን ይህም ለአገልግሎቱ ከፍተኛ ተግዳሮት ሆኖበት ይገኛል፡፡ ማእከሉ ሓላፊነት የወሰድንበት ትውልድ የማዳን የቤተ ክርስቲያን አደራ በአግባቡ ለመወጣት የማዕከሉን ሁለንተናዊ የማስፈጸም አቅም ማሳደግ ወሳኝ በመሆኑ የውስጥን አቅም ለማሳደግ ከተያዙት በርካት ተግባራት መካከል ለቤተ ክርስቲያን እና ለማኅበሩ አገልግሎት ብሎም ለሀገር ከፍተኛ አስተዋጽኦ ይኖረዋል ተብሎ የሚጠበቀው የማዕከላችን ሁለገብ የአገልግሎት እና ቋሚ ገቢ ማስገኛ 2B+G+12 የሕንጻ ግንባታ ፕሮጀክት አንዱ ነው፡፡

ፕሮጀክቱን በተመለከተ የማእከሉ ሥራ አስፈጻሚ ጉባኤ የፕሮጅክቱን አስፈላጊነት በጥናት ከመረመረ በኋላ መጋቢት 6, 2011 ዓ.ም የፕሮጀክቱን ዓብይ ኮሚቴ በማቋቋም ቀጣይ ጥናቶችን በማድረግ በማእከሉ የአባላት ጠቅላላ ጉባዔ ላይ በማስወሰን ሐምሌ 13, 2011 ዓ.ም የፕሮጀክቱን ሥራ በይፋ አስጀምሯል፡፡

በመሆኑም ማእከሉ "እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ነገን እንቅድመው!!!" በሚል መሪ ቃል "የሰማይ አምላክ ያከናውንልናል እኛም ባሪያዎቹ ተነስተን እንሠራለን፡፡"ነህ 2፥20፣ የሚለውን የቅዱስ መጽሐፍን ኃይለ ቃል አንግቦ ይህን ሁለገብ የአገልግሎት እና ቋሚ ገቢ ማስገኛ ሕንጻ ፕሮጅክት ተግባራዊ ለማድረግ እስካሁን የቦታ ግዥ፣ የዲዛይን ስራ፣ ይዞታ የማስከበር፣ የግንባታ ፍቃድ ማውጣት፣ ለመሠረት የሚሆን ብረት ግዥ በመፈጸም እና ቦታውን ለመሠረት ሥራ ዝግጁ በማድረግ ተግባራዊ እንቅስቃሴ አድርጓል፡፡



የአ/አ ማእከል የአገልግሎት እና የቋሚ ገቢ ማስገኛ ሕንጻ



ለሕንጻ ግንባታ ዝግጁ የሆነ ባለ 500 ካሬ ሜትር ቦታ

## የፕሮጀክቱ ፋይዳ

1.የወጣቶችን ሁለንተናዊ ሰብእና ማበለጸጊያ ማእከል ለማቋቋም፣

2. ለአገልግሎት ምቹ ሁኔታ በመፍጠር ማእከሉ አሁን እየሰጠ ያለውን አገልግሎት በብዙ እጥፍ ያሳድገዋል፣

3. ግቢ ጉባኤያት እና ወረዳ ማእከላት ያለባቸውን የአገልግሎት ቦታ እጥረት በዘለቄታነት ይፈተዋል፣

4. ቋሚ የገቢ ማስገኛ በማድረግ ኢኮኖሚያዊ አቅም ማሳደግ፣

5. ማእከሉ ቋሚ የግል ሃብት ይኖረዋል ለሌሎች ኢንቨስትመንቶች መነሻ ሃብት ይሆናል፣

6. ማእከሉ ስብከተ ወንጌልን ለማስፋፋት፣ ገዳማት እና አብነት ት/ት ቤቶችን ለመደገፍ እና የአባላቱን የአገልግሎት ተሳትፍ ለማሳደግ ፕሮጀክቱ ከፍተኛ ፋይዳ ይኖረዋል፡፡



የአዲስ አበባ ማእከል ሕንፃ ዲዛይን